# ለታላቁ ቃለ ዓዋዲ

# (የአዋጅ ቃል)

# ቀዳሚ መልእክት!

## ይድረስ፡-

## "ኢትዮጵያውያን እና ኢትዮጵያውያት ነን!"

## ለምትሉ ወገኖች!

## እንዲሁም፡

## ለሰው ልጆች ኹሉ!

**ኢትዮጵያዊዉን ሰላምታችንን እናቀርብላችኋለን።**

**እግዚአብሔር፡ ምስጋና ይድረሰውና፡ ለእናንተ እና በእናንተ፥ ስለእናንተም፡ ሊያደርግ ያቀደውን ዕፁብ ድንቅ ሥራውን ኹሉ አከናውኖ ጨርሷል፤ የቸርነትና የምሕረት ስጦታውንም ኹሉ ሰጥቶ አብቅቷል፤ የቀረው፡ አንዳችም ነገር የለም።**

**የቀረ ነገር ቢኖር፡ የእናንተ ድርሻ ብቻ ነው። ያም ድርሻችሁ፡ ይህን ኹሉ፡ የተትረፈረፈ ስጦታውን ተቀብላችሁና በዚያ ተጠቅማችሁ፡ እየራሳችሁን፡ ለመልካሙ የሕይወት ህልውና (አኗኗር) ማብቃት ነው።**

ስለዚህ፡ እንደእናንተ፡ ሰው የኾነው እግዚአብሔር፡ "በዚህ መልእክት፡ የምላችሁን ስሙኝ!" ይላችኋል።

እናት አገራችን ኢትዮጵያ የኾነችው፡ እናቱ ድንግል ማርያምም፥ "ወትቤሎሙ እሙ፡ ለእለ ይትለአኩ፡ 'ኵሎ ዘይቤለክሙ ግበሩ!' ብላ፡ ለቃና ዘገሊላ፡ የሠርግ አገልጋዮቻቸው እንደተናገረች፡ ዛሬም፡ ለእናንተ፡ "ልጄ፡የሚላችሁን ኹሉ፡ ስሙት! አድርጉትም!" ትላችኋለች። (ዮሐ. ፪፥ ፭።)

እንግዴህ፡ ልጁ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ የሚላችሁ፡ ይህ ነውና፡ ስሙት! "‹እነሆ፡ ማደሪያዬ ይኾን ዘንድ፡ ሰውነታችሁ፡ ይኸውላችሁ! እንካችሁ!› ብዬ ሰጠኋችሁ። እርሱም፡- በመጀመሪያ፡ ግዙፍ የኾነውንና በደመ ነፍስ የሚንቀሳቀሰውን፡ እንስሳዊ የሥጋን አካልና ባሕርይ የተላበሳችሁት፥ ከምድር አፈርም አሳምሬ ያበጀሁት ነው፤

ከዚያ ቀጥሎ፡ 'በመልኬ ፈጠርሁት!' ያሰኘችኝንና የምንነቴ መታወቂያ የኾነችውን፡ የነፍስን አካልና ባሕርይ፡ እፍ ብዬበት፡ እንደእኔ ሕያው ያደረግሁት ነው፤

በመጨረሻ፡ 'ከእኛ፡ እንደአንዱ ኾነ!' ያልሁበትንና የማንነቴ መለያ የኾነውን፥ ደጉንና ክፉውንም የሚያሳውቀውን፥ ከኹለቱ፡ አንዱን መርጦ ለመወሰንና አጽንቶ ለማስፈጸም የሚያስችለውን፡ የመንፈስን አካልና ባሕርይ ያቀዳጀሁት ነው።

"በዚህ ምንነታችሁና ማንነታችሁ፡ ከሓሰት ይልቅ፡ እውነትን፥ ከክፋት ይልቅ፡ ደግነትን፥ ከሞት ይልቅ፡ ሕይወትን በመምረጥ፡ እኔን መስላችሁ፥ እኔን አኽላችሁ፡ በመልካም ኑሩበት!" ብሎ፡ የነፍስ፥ የሥጋና የመንፈስ ሦስትነታችሁን፡ በምሥጢረ ተዋሕዶ፡ ፍጹም አንድ አድርጎ፡ ሰብአዊነትን ሰጣችሁ።

በዚህ ሰውነታችሁ፡ ለዘለዓለም የምትኖሩባትን፡ የምድር ገነትንም፡ አኹን በምታዩት ዓለም፡ እንዲህ አዘጋጅቶና አሟልቶ፡ ወደእርሷ አምጥቷችሁ፡ ይኸው፡ እየተመላለሳችሁባት ትገኛላችሁ!

ታዲያ! በቅድሚያ፡ እናንተ፡ ይህን፡ የሰውነታችሁን ትክክለኛ ምንነትና ማንነት እንኳ፡ ሳታውቁትና ሳትጠቀሙበት፥ ሳትደሰቱበትና ሳትሠሩበትም፡ እንዲያው፡ ዝም ብላችሁ፡ በሥጋ፥ በነፍስና በመንፈስ ባደረጋችሁት፡ የክፋት፥ የኃጢአትና የሞት ምርጫችሁ ብቻ እየተመራችሁ፡ በሥቃይ ኑሮ የምትኳዙት፡ ለምንድር ነው? እስከመቼስ ነው?

ቀጥሎም፡ እርስ በእርሳችሁ፡ "ወንድና ሴት፥ ሽማግሌና ወጣት፥ ሥጋዊና መንፈሳዊ፥ ካህንና ምእመን፥ ጻድቅና ኃጥእ፥ ቅዱስና ርኩስ፥ አዋቂና አላዋቂ፥ ማይምና ምሁር፡ (ያልተማረና የተማረ)፥ ተማሪና ወታደር፥ የበላይና የበታች፥ ገባርና አስገባሪ፥ ነጋዴና ቀራጭ፥ ከተሜና ገጠሬ፥ ጨዋና ባለእጅ፥ ሠሪና አሠሪ፥ አገልጋይና ተገልጋይ፥ ትልቅና ትንሽ፥ ደኃና ሀብታም፥ ገዢና ተገዢ፥ ፈራጅና ተፈራጅ፥ ነጭና ጥቁር፥ ቀይና ጠይም፥ ሴማዊና ካማዊ፥ ያፌታዊና አበሻ፥ አረማዊና ቡድሃዊ፥ አሕዛብና ሕንዳዊ፥ አይሁዳዊና ሳምራዊ፥ ክርስቲያንና እስላም፥ አማኒና ኢአማኒ!" እየተባባላችሁ፡ ተለያይታችሁ፡ በጠላትነት የምትኖሩት፡ ለምንድር ነው? እስከመቼስ ነው?

በመጨረሻም፡ ቸሩ ፈጣሪያችሁ፡ "ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ናትና፡ እንካችሁ ኑሩባት! ተገልገሉባት! አገልግሉባትም" ብሎ፥ ቤተ ሕዝቡን፥ ቤተ ምልክናውንና ቤተ ክህነቱን፡ በምሥጢረ ተዋሕዶ፡ አከናውኖና አንድ አድርጎ፡ ከመጀመሪያዎቹ ፍጡሮቹ፡ ከአዳምና ሔዋን ጀምሮ፡ የሰጣችሁን፡ የሕይወትና የህልውና ሥርዓት፡ ለውጣችሁ፡ በሰይጣናዊው ስሑት ልማድ፡ "ቤተ ክህነት እና ቤተ መንግሥት፥ ሃይማኖትና አገዛዝ (Church and State፣ እምነትና ፈሊጥ [ቦለቲካ])" እያላችሁ፡ ከፋፍላችሁ፡ ይኸው፡ እስከመጋደል ባደረሳችሁ፡ የማያባራ ጠብና ጦርነት ውስጥ ተዘፍቃችሁ፡ መተላለቃችሁን የምትቀጥሉት፡ ለምንድር ነው? እስከመቼስ ነው?

ፍጥረት፥ በተለይም፡ የሰው ዘር፥ ይልቁንም፡ "ኢትዮጵያዊ እና ኢትዮጵያዊት ነን!" የምትሉት እናንተ፡ ከቶ፡ ምን እስኪመጣ፥ ምንስ፡ እስኪኾን እየጠበቃችሁ ነው? እንደመለኮታዊው የትንቢት ቃል፡ በኖኅ ዘመን የደረሰውን የመሰለው፥ ነገር ግን፡ እንደቀደመው፡ በውኃ ሳይኾን፡ በእሳት የሚኾነው፡ የአኹኑ፡ አጠቃላዩና ደምሳሹ የጥፋት ማዕበል እስኪመጣ ነው፡ እየጠበቃችሁ ያላችሁት?

በሉ እንጂ! ለኹሉም ጥያቄ፡ መልሱን ስጡ! ዝም አትበሉ! በእየራሳችሁ፥ የእናንተም በኾኑት፥ በሌላውም ላይ ምን እስኪኾን፥ ምንስ እስኪመጣና እስኪደርስ ነው፡ እየጠበቃችሁ ያላችሁት?

**የእግዚአብሔር ባልኾነው፡ በተቃራኒው ቀንበር ተጠምዳችሁና በአላዋቂነቱ ጨለማ ተሸፍናችሁ፡ እስከዛሬ፡ በዕውርነትና በግዞተኝነት የቀጠላችሁበትን፡ ይህን፡ የግብዝነት አኗኗራችሁን፡ አኹንና ወደፊትም፡ የመቀጠል ቍርጥ ፍላጎት ያላችሁ ናችሁን?**

**<u>አዎን! ምርጫችሁና ፍላጎታችሁ፡ ይህ መኾኑን፡ እነሆ፡ ዛሬ የምትገኙበት፡ የኹላችሁም አቋም፡ እያረጋገጠ ይመሰክራል።</u>**

**ስለዚህ፡ ይኸው ነባራዊው ኹኔታችሁ፡ በዚህ፡ በመጨረሻው ዘመን፡ በእግዚአብሔር እውነትና ብርሃን፡ እነሆ፡ ተከሥቷልና፡ እያንዳንዳችሁ፡ በነፍስ ወከፍ፡ ለእየራሳችሁ መልካም ሕይወት ስትሉ፡ ለጥቂት አፍታ፡ በያላችሁበት፡ ቆም፥ ወይም፡ ዐረፍ ብላችሁ፥ የኅሊናችሁንም ዓይን ገልጣችሁ፡ በማስተዋል ትመለከቱት ዘንድ፥ ካላዋቂነት ሰመመናችሁም ነቅታችሁ፡ የፈጣሪያችሁንና የእናቱን ቃል፡ በተመስጦ ታደምጡ ዘንድ፡ ይህን ታላቅ፡ የቃለ ዓዋዲ፡ ቀዳሚ መልእክት አቅርበንላችኋል!**

---

## መግቢያ

ባለፉት ዓሠርት ዓመታት፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት አገልጋይ፡ በንቡረ እድ ኤርምያስ ከበደ ወልደ-ኢየሱስ አማካይነት ተዘጋጅተው፡ እስካኹን፡ በተሠራጩት መጻሕፍታችንና በኅዋ ሰሌዳችን ገበታዎች አማካይነት በተላለፉት የእግዚአብሔር መልእክቶች፡ ስለኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት፥ ስለኢትዮጵያዊውና ኢትዮጵያዊቷ ማንነትና ምንነት፡ በስፋትና በምልዓት፥ በጥልቀትና በምጥቀት፥ በጽሙናና በይፋ፥ በዝርዝርና በማጠቃለል፡ በሚበቃ ተነግሯል፤ ተጽፏል፤ ተብራርቷል፥ ታትቷል።

ይህንም ንግግርና ጽሕፈት፥ ማብራሪያና ሓተታ፡ እንኳንስ፡ "ዘመናዊዉን የሥልጣኔ ትምህርት አግኝቼ አውቄአለሁ!" የሚለው፡ የዛሬው ትውልድ ይቅርና፡ በድንጋይ ዳቦ ጊዜ በነበረው መልክና ይዘት፡ በየዳር አገሩ፥ በየዱር ገደሉም ተገልለው፡ "ጥሬ" በሚባለው፡ የጥንተ ተፈጥሮ ሥርዓት የሚኖሩ የሰው ወገኖች እንኳ፡ በቀላሉ ሊገባቸው ይቻላቸዋል። ይህን እውነታ፡ ከማወቅና ከመረዳት አልፎ ለመገንዘብ ያልተቻለው፥ ወይም፡ የማይችል ሰብአዊ ፍጡር ካለ፡ "የተፈጥሮ ጕድለት ያለበት ደካማ ወይም፡ ራሱን፡ ለስንፍና የዳረገ፥ ያዋቂ-አጥፊ ነው!" ከማለት በቀር፡ ሌላ ትርጕም ሊሰሰጠው፥ ወይም፡ ምክንያት ሊቀርብበት የሚያስፈልግ አይኾንም።

በዚህ ረገድ፡ ይህ ትውልድ፡ እግዚአብሔር፡ በነቢዩ አንደበት፡ **"ወይመስሉ ሕዝብየ፡ ከመ ዘአልቦ ልብ። እስመ ለከሂ ኃደገከ ልብከ፤ ወአነሂ፡ ኃደግሁከ፤ ኢትሡዕ ሊተ፣ እስመ ረሳዕከ ሕገ አምላክከ!"** ማለትም፡ **"ሕዝቤ ሆይ! በተፈጥሮ ያደልሁህን፡ የልቦናህን እውቀት ትተህ፡ አእምሮ እንደሌለው ሰው ኾነሃልና፥ የአምላክህንም ሕግ ረስተሃልና፡ እኔም፡ በረድኤት ተለይቼሃልሁ፤ አትሠዋልኝ!"** ብሎ ለተናገረው መለኮታዊ ቃል፡ የተዳረገ ኾኖ ይገኛል። (ሆሴዕ ፬፥ ፮።)

## ይህ መልእክት ያስፈለገበት ምክንያትና ዓላማው።

በአኹኑ ጊዜ፡ ይህ መልእክት እንዲተላለፍ አስፈላጊ የኾነበትን ምክንያት፡ እንደሚከተለው፡ ባጭር እንግለጥላችሁ!

የእግዚአብሔር መንግሥት የኾነችው ኢትዮጵያ፡ ለታማኞች ልጆቿ ተገልጻ፥ እነርሱም እየኖርዋትና እያገለገሏት፡ እስከዛሬ፡ ለሰባት ሺህ አምስት መቶ አምስት ዓመታት፡ በነጻነት ህልውናዋ ያለች፥ አኹንም፡ በእነርሱ ዘንድ፡ በዚያው በሕያው ነጻ አቋሟ የቀጠለች መኾኗ ይታወቃል።

ይህች፡ ስመ ጥሩዪቱና ገናናዪቱ **ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡** ከጥንት ከመሠረት፡ እጆቿን ወደእግዚአብሔር፡ ያለማቋረጥ ዘርግታ፡ ለሰው ዘርና ለፍጥረተ-ዓለሙ ኹሉ የማለደችው ናት፤ ምልጃዋም፡ በእግዚአብሔር አብ ዘንድ ተቀባይነትን አግኝቶ፡ ተቀዳሚና ተከታይ የሌለውን፡ አንድ ልጁን፡ ወደእርሷ ልኮ፡ በሰውነት ትወልደው ዘንድ ፈቃዱ የኾነላት፥ ራሷንም፡ ለአምላክ እናትነት ያበቃችው የመለኮት ሙሽራ ናት፤ በዚህ ሙሽርነቷም፡ የጠፋውን የሰውን ዘርና ፍጥረተ ዓለሙን ኹሉ፡ ከክፋት እና ከጥፋት፥ ከኃጢአት እና ከሞት፡ ለዘለዓለሙ፡ በቤዛነቱ ሊያድን፡ ወደዚህ ዓለም የመጣውን፡ የእግዚአብሔርን ልጅ፡ ኢየሱስ ክርስቶስን የወለደችው፡ **ቅድስት ድንግል ማርያም ናት።**

እንግዴህ፡ **"ወይሰበክ ዝ ወንጌለ <u>መንግሥተ እግዚአብሔር</u> ውስተ ኵሉ ዓለም፤ ከመ ይኩን ስምዐ ላዕለ ኵሉ አሕዛብ፤ ወይእተ አሚረ ይበጽሕ ኅልቀት!"**

ማለትም፡ **"በአሕዛብ ኹሉ ላይ ምስክር እንዲኾን፡ ይህ፡ <u>የእግዚአብሔር መንግሥት</u> ምሥራች፡ በዓለም ኹሉ ይሰበካል! በዚያን ጊዜ፡ መጨረሻው ይመጣል።"** ባለው፡ በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መለኮታዊ ቃል መሠረት፡ ይህችው ኢትዮጵያ፡ በቃልና በመጽሓፍ ብቻ ሳይኾን፡ በኀዋ ሰሌዳዎች ልዩ ልዩ መድረኮች ላይ ሳይቀር፡ **<u>"ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት!"</u>** በሚለው ስሟና ማንነቷ፡ ለመላው ዓለሙ ኹሉ እየታወጀች መኾኗ፡ ይኸው፡ በይፋ በሚታየው ተጨባጭ እውነታ ተረጋግጦ ይነበባል።

ከዚህ የተነሣ፡ ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ ባላመነው፡ ሥጋዊ ዓለም ዘንድ ተገልጻ የምትሰፍንበት ጊዜ በመቃረቡ፡ ባጠቃላይ፡ እያንዳንዱ ሰብአዊ ፍጡር፥ በተለይም፡ "ኢትዮጵያዊ፥ ኢትዮጵያዊት ነኝ!" የሚለው ወገን፡ ይህን፡ ግዙፍ የኾነ እውነታ፡ በማስተዋል ተመልክቶ፡ ለራሱ፡ ምድራዊና ሰማያዊ ደኅንነት ሲል፡ በቶሎ፡ የየግሉን ማንነትና ምንነት በማስተካከል፡ እየራሱን እንዲያዘጋጅ፡ አምላካዊው የማስጠንቀቂያ ጥሪ፡ እየተጠናከረለት መጥቷል፤ በባለቤቱ በእግዚአብሔር ዘንድ፡ ወንዱ ኹሉ፡ "ገብር ኄር" ማለትም፡ "ታማኙ አገልጋይ!" የተባለውን ጕበዝ፥ ሴቷም ኹላ፡ ሙሽራውን ሊቀበሉ ከተመረጡት ደናግል መካከል፡ "ልባሞች!" የተባሉትን ደንገጥሮች መስለው ይገኙ ዘንድ። (ማቴ. ፳፬፥ ፲፬።)

አዎን! የዚህ ታላቅ፡ የአዋጅ ቃል መልእክት ዋና ዓላማ፡ ይህን፡ አምላካዊ የማስጠንቀቂያ ጥሪ፡ ለሚመለከተው ኹሉ ለማድረስ፥ ለማስታወስና ለማሳሰብ ነው።

እንዳስተዋላችሁት፡ በዮሐንስ ራእይ ላይ፡ "፮-፳፮"፥ ወይም፡ "፮፻፳፮" የሚለው አኀዝ የተሰጠው "የጥፋት ርኵሰት" መታወቂያ ቊጥር፡ ፮ኛ ወር በኾነው፡ በየካቲት ወር፥ ፲፱፻፳፮ ዓመተ ምሕረት፡ በኢትዮጵያ፡ በገሃድ ከተገለጠ፡ እነሆ፡ አርባ ዓመታትን እያስቆጠረ ይገኛል፤ የዚህ የኢትዮጵያ ትውልድ ጽኑ መከራ፡ በዚህ ረዥም ጊዜ ውስጥ፡ ማብቃቱ ቀርቶ፡ እየረቀቀና እያየለ፥ እየደረጀና እየተንሠራፋ ከመኼድ በቀር፡ የመቀነስ፥ ወይም የመርገብ ምልክትን እንደማያሳይ፡ ይኸው፡ በይፋ የሚታይ ኾኗል። ለምን? ምክንያቱ፡ እንደሚከተለው፡ ግልጽ ነው።

በአገር ውስጥም ኾነ፡ በውጭው አህጉር ያለው፡ ይኸው የኢትዮጵያ ትውልድ፡ ተጠቃልሎ የሚገኝባቸው፡ ቤተ ሕዝቡ፥ ቤተ ምልክናውና ቤተ ክህነቱ፡ ኹሉም፡ በትስብእት ደም ታትሞ በጸናው፥ እውነተኞቹ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያትም፡ እስከዛሬ ጠብቀውት በኖሩት፡ በቅዱሱ ኪዳን ላይ ከፈጸሙት፡ ከታላቁ የክህደትና የዓመፅ፥ የክፋትና የአመንዝራነት ኃጢአታቸው ምክንያት፡ በመለኮታዊው ውግዘት እንደተያዙ ቀጥለውበታል።

እኒሁ ወገኖች፡ ከዚህ ታላቅ ኃጢአታቸው፡ በእውነተኛ ንስሓ ተመልሰው፡ ውግዘቱ እንዳይፈታላቸው፡-

መጀመሪያ፡ ከፈጣሪያቸውና ከቅድስት እናቱ፡ ይቅርታ መጠየቅን፡ በትዕቢትና በዕብሪት፥ በትምክህትና በማናለብኝነት "እምቢ!" ብለው፡ በአንገተ ደንዳናነት እንደጸኑ ይገኛሉ።

ዳግመኛ፡ እርስ በርሳቸው፡ ይቅር መባባልን፡ እንደዚሁ፡ "አሻፈረን!" ብለው፡ በጠላትነት መቀዋወማቸውን ቀጥለውበታል።

በመጨረሻም፡ በእየራሳቸው ውስጥ፡ የሰላምና የፍቅር፥ የመግባባትና የስምምነት ስሜት የሌላቸው መኾናቸውን፡ በዚሁ መራራ ፍሬያቸው አረጋግጠው አሳውቀዋል።

በአምላካዊው ቃል፡ "**ትውልድ ዕሉት ወዓማፂት፥ ዕክይት ወዘማዊት**" ማለትም፡ "**ከሃዲና ዓመፀኛ፥ ክፉና አመንዝራ ትውልድ**" የተባለችውንና ክርስቶስን ሰቅላ የገደለችውን፡ የአይሁድን ትውልድ የመሰለው፡ ይኸው የዛሬው፡ የኢትዮጵያ ትውልድ፡ ከዚህ ኃጢአቱ፡ በንስሓ የመመለስ አዝማሚያ ሊይታይበት፡ ፈጽሞ ያልተቻለ በመኾኑ፡ ከፈተናው እሳትና ከመከራው ማዕበል፡ ምንም ያህል እንዳልተማረ አስመስክሯል። (ማቴ. ፲፪፥ ፴፱።)

ከላይ እንደተመለከተው፡ ጊዜው ከማለፉና ቀኑ ከመምሸቱ በፊት፡ ይህን፡ መለኮታዊ የኾነውን፡ የመጨረሻ፡ የጥሪ መልእክት፡ **ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡** ባጠቃላይ፡ ለእያንዳንዱ ሰብአዊ ፍጡር፥ በተለይም፡ "ኢትዮጵያዊ፥ ኢትዮጵያዊት ነኝ!" ለሚለው ወገን፡ በነፍስ ወከፍ አቋሙ፡ የእየራሱን ውሳኔ ይሰጥበት ዘንድ፡ እንድታቀርብለት፡ የግድ አስፈላጊ ኾኖ የተገኘው፡ በዚህ ምክንያት መኾኑ፡ ሊሠመርበት ይገባል።

## ይህን፡ የመጨረሻውን መለኮታዊ ጥሪ ሰምቶ ለመቀበል።

**ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት** ያቀረበችውን፡ ይህን ጥሪ ለመቀበል፡ በቅድሚያ፡ እያንዳንዱ ወንድ እና እያንዳንዷ ሴት፡ በኢትዮጵያና በኢትዮጵያዊነት ረገድ፡ ኹለቱም ጾታዎች፡ በእየራሳቸው፡ ስለእየራሳቸው እውነተኛ ማንነትና ምንነት፡ ሊያውቋቸው የሚገባቸውን፡ መሠረታውያን የእግዚአብሔር እውነቶች፡ እንደሚከተለው፡ አንድ በአንድ ዘርዝረን ስለምናቀርብ፡ በትኵረትና በማስተዋል መከታተሉ፡ የእየአንዳንዳችሁ ፈንታ መኾኑን፡ አስቀድመን እናሳስባለን።

ይህ ግዳጅ በሚፈጸምበት ጊዜ፡ እያንዳንዳችሁ ግለሰቦች፡ ወደፊትና ወደኋላ፥ ወደቀኝና ወደግራ፥ ወደላይና ወደታች፥ ዙሪያችሁንም፡ በቅርብና በሩቅ መመልከት፡ ፈጽሞ አያስፈልጋችሁም፤ አዎን! ወደማንኛውም ዓይነት ሰው፡ ሴትም ኾነች ወንድ፡ ማተኮርና ስለማንኛውም ዓይነት ሰው፡ ማሰብም ኾነ መናገር፡ ከቶ አያስፈልጋችሁም፤ ለመልካም አርአያነት የሚጠቀስ፡ ዛሬ፡ በአካለ ሥጋ፡ ሕያው የኾነ፡ ሌላ ሰብአዊ ፍጡር የለምና፤ **በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት፡ በውስጣችሁና በመካከላችሁ ከሚገኙት፡ ከኢየሱስ ክርስቶስና ከድንግል ማርያም በስተቀር።**

በአካለ ነፍስ፡ በተመስጦ ማሰብ፥ በአካለ ሥጋ፡ በጽሙና ማድመጥና በአካለ መንፈስ፡ በአትኵሮት መመልከት የሚያስፈልጋችሁ፡ ወደእየራሳችሁ ውስጣዊ ሰውነት ብቻ መኾን ይኖርበታል። ምክንያቱም፡ ምድራዊና ሰማያዊ፥ ጊዜያዊና ዘለዓለማዊ የኾነው፡ የግላዊው ሕይወታችሁ፥ ወይም ሞታችሁ፡ ዓቢይ ጉዳይ የሚወሰንበት የፍርድ አደባባይ፡ ያ፡ እግዚአብሔር፡ ያለማቋረጥ የሚገኝበትና የየግለሰብእናችሁ፡ የሥጋና የነፍስ ማዕከል የኾነው፡ "ኅሊና" የሚባለው ውስጣዊ ሰውነታችሁ፡ ማለትም፡ መንፈሳችሁ በመኾኑ ነው።

በዚህ መርሕ መሠረት፡ የእየራሳችሁን ማንነትና ምንነት፡ በትክክል ለማወቅ የምታደርጉትን ጕዞ፡ በደኅና አካኺዳችሁ፡ ከደገኛው ግብ ለማድረስ የሚቻላችሁ፡ በእግዚአብሔር የእውነትና የብርሃን ፋና መሪነት በመኾኑ፡ ለዚህ ለተነሣንበት፡ ለታላቁ ቀዳሚ፡ የአዋጅ ቃል መልእክታችን ዓላማ መከናወን፡ የሚያስፈልጋችሁ ዝግጅት፡ እንዲህ በሚል አጭር ዐረፍተ ነገር ይጠቃለላል፡-

**<u>የራስን አፍአዊና ውሳጣዊ ሰውነት፡ በእውነትና በመንፈስ ቅዱስ አምልኮ፡ ንጹሕ አድርጎ መገኘት።</u>**

ነቢዩ፡ "**ፈኑ ብርሃነከ፥ ወጽድቀከ! እማንቱ ይምርሃኒ፥ ወይሰዳኒ፡ ደብረ መቅደስከ።**" ማለትም፡ "[እግዚአብሔር ሆይ! በአንተ ሥርዓት፡ መልካሙን ሕይወት መኖር እንድችል ወደሚያበቃኝ] **ወደመቅደስህ ተራራ መርተው ይወስዱኝ ዘንድ፡ ብርሃንህንና እውነትህን ላክልኝ!**" ሲል እንደጸለየው። (መዝ. ፵፪፥ ፫።)

ይህን ታላቅ መልእክቷን፡ ወደባለአድራሻዎቹ፡ ወደእናንተ እያደረሰች ያለችው፡ ይህችው፡ **ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡** ከዚህ በኋላ፡ ወንዱን፡ "አንተ!"፥ ሴቲቱንም፡ "አንቺ!" እያለች የምታመለክተው፡ በነፍስ ወከፍ፡ እናንተኑ፡ እየራሳችሁን መኾኑን፡ አስቀድማችሁ እንድታውቁት ይኹን።

## ኢትዮጵያዊነት፡
## የምንነታችሁና የማንነታችሁ መታወቂያ ስለመኾኑ።

ይህን የአቀራረብ ሥርዓት በመከተል፡ አኹን፡ የመልእክቱን ቍም ነገሮች እየዘረዘርን መግለጽ እንጀምራለን፡-

፩ኛ፤ "የአንተ እና የአንቺ <u>"ምንነት እና ማንነት"</u> ምንድር ነው?" ለሚለው ጥያቄ፡ መልሱ፡ የሚከተለው ነው፡-

ይህ፡ የአንተ እና የአንቺ <u>"ምንነት እና ማንነት"</u>፡ በአጠቃላይ ኹለንተናው፡ ተለይቶ የሚታወቅበት ህልውና፡ <u>"ኢትዮጵያዊነት"</u> ነው፤ <u>"ኢትዮጵያዊነት"</u>፡ በማይናወጠው መሠረታዊ ዐለትነቱና በጽኑው ግድግዳዊ አቋምነቱ፥ በዘለዓለማዊው ማኅተም በተደመደመው ጕልላትነቱም፡ ተከሥቶለትና አውቆት ይኖረው ዘንድ፡ ቸሩ ፈጣሪ፡ ራሱን አስመስሎ ለፈጠረውና ለወደደው ሰብአዊ ፍጡሩ ኹሉ የሰጠው፡ **የህልውና መገለጫ ነው።**

"**ኢትዮጵያዊነት**"፡ በዚህ መገለጫነቱ፡ የሰው ትምህርትና ሥርዓት፡ በሰው ልጆች ህልውና ላይ ያደረሱትን፡ እነዚያን፡ በአርእስቱ የተዘረዘሩትን፡ የክፍፍልንና የመለያየትን ጠንቆች አስወግዶ፡ "**ዘእግዚአብሔር አስተፃመረ፣ ሰብእ ኢይፍልጥ!**" ማለትም፡ "**እግዚአብሔር፡ አንድ ያደረገውን፡ ሰው አይለየው!**" ወደሚለውና የእግዚአብሔር ልጆች ይኖሩበት ዘንድ፡ "**የእግዚአብሔሩ እውቀትና ሥርዓት**" ተብሎ ወደተሰጠው፡ ወደቅዱሱ ኪዳን አንድነቱ መልሶ አዋሕዶታል። (ማቴ. ፲፱፥ ፮።)

የዚህ ኢትዮጵያዊነት ምሥጢር፡ በዚህ ብቻ የተወሰነ አይደለም። እግዚአብሔር፡ ይህን ግዙፍ ዓለም በፈጠረ ጊዜ፡ ቤተ ሕዝቡን፥ ቤተ ምልክናውንና ቤተ ክህነቱን አዋሕዳ የያዘችውን፡ የዘለዓለም መንግሥቱን፡ ገሃድ ያደረገበት ሥርዓት ነው፡ ይህ **ኢትዮጵያዊነት**፤ በመልኩ የፈጠራቸውን፡ አዳምንና ሔዋንንም፡ በዚች መንግሥቱ ላይ የሠለጡኑ፡ የመጀመሪያዎቹ ወንድና ሴት፥ ባልና ሚስት፥ አባትና እናት፥ ካህንና ካህኒት፥ ንጉሥና ንግሥት እንዲኾኑ የሠየመበት ነው፡ ይህ **ኢትዮጵያዊነት**። እግዚአብሔር፡ እነርሱን፡ ለዚህ ማዕርግና ሥልጣን ያበቃቸው፥ ሥርዓቱንም የመሠረተው፡ በዚህ **ኢትዮጵያዊነት** እንደነበረ፡ የቅዱሱ ኪዳን ሃይማኖታችን አረጋግጦ አሳውቆናል።

ይህ ሥርዓት፡ እስከዛሬ ጸንቶ እንደቀጠለ ኹሉ፡ ወደፊትም፡ ለዘለዓለም እንደማያቋርጥ፡ የዚህ ማረጋገጫ፡ አንዱ ዓይነተኛ ገጽታው ኾኖ ያመለክተናል። ይህም ገጽታ፡ **ኢትዮጵያዊነት**፡ እግዚአብሔር፡ ጥንቱኑ፡ ዓለምን ሲፈጥር፡ እንዲህ፡ ሰውን ለሚያስቀድመው፡ ለፍጥረተ ዓለሙ፡ መነሻ ብቻ ሳይኾን፡ መንደርደሪያውም፥ በፍጻሜውም፡ ግቡ አድርጎ ያዘጋጀው ዕቅዱ መኾኑን የሚያሳየው እውነታ ነው።

እግዚአብሔር፡ ይህን የኢትዮጵያዊነት ሥርዓት፡ በመጀመሪያው ዘመን፡ በአዳም እና ሔዋን ማንነትና ምንነት፡ ማለትም፡ በቀዳሚዎቹ ወንድና ሴት፥ ባልና ሚስት፥ አባትና እናት፥ ካህንና ካህኒት፥ ንጉሥና ንግሥት፡ መሠረተው፤ ከሠተውም።

ኋላም፡ እርሱ፡ ኢትዮጲስ፡ በማዕርግ ስሙ፡ "መልከ ጼዴቅ" ተብሎ፥ እርሷ፡ እንተላ፡ በማዕርግ ስሟ፡ "ሳሌም" ተብላ፡ በመካከለኛው ዘመን በተገለጹት፥ በእኒህ፡ በማዕከለኞቹ ወንድና ሴት፥ ባልና ሚስት፥ አባትና እናት፥ ካህንና ካህኒት፥ ንጉሥና ንግሥት፡ አጽንቶ ቀጠለው።

በመጨረሻውም ዘመን፡ እርሷ፡ ድንግል ማርያም እና እርሱ፡ ልጇ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ መደምደሚያዎቹና አማናውያኑ አባትና እናት፥ ካህንና ካህኒት፥ ንጉሥና ንግሥት ኾነው፡ የኢትዮጵያዊነትን ሥርዓት በዘለዓለማዊነት ፈጸሙት።

አዎን! በዚህ ሥርዓት፡ ድንግል ማርያም፡ በማዕርግ ስሟ፡ "ኢትዮጵያ፥ መርዐተ አብ፥ ወእመ በግዑ [የአብ ሙሽራና የልጁ እናት]፥ ወላዲተ አምላክ [የአምላክ እናት]፥ አማናዊቷና ዘለዓለማዊቷ ሔዋን፥ የሕይወት ዛፍ፥ ደብረ ጽዮን [የጽዮን ተራራ]፥ ኢየሩሳሌም፥ ጽላተ ኪዳን፥ ቤተ መቅደስ፥ ንግሥተ ሰማያት ወምድር [የሰማይና የምድር ንግሥት]፥ ኪዳነ ምሕረት" ተባለች፤ እርሱ፡ ልጇ፡ ኢየሱስ ክርስቶስም፡ በፈጣሪነቱና በአምላክነቱ፡ "ወልደ-እግዚአብሔር [የእግዚአብሔር ልጅ]፥ ቃለ-እግዚአብሔር [የእግዚአብሔር ቃል]"፥ በትስብእቱም፡ "የሰው ልጅ፥ የእግዚአብሔር በግ፥ መድኃኔ ዓለም [የዓለም መድኃኒት]፥ የፋሲካ በግ፥ አማናዊውና ዘለዓለማዊው አዳም፥ የሕይወት ዛፍ ፍሬ" ተባለ።

# የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት
## በኦሪታውያኑ እስራኤላዊነትና በግብፃውያኑ ኦርቶዶክሳዊነት
## የተካኼደበት ጥቃት።

እውነተኛው፡ የአይሁድ ኦሪታዊ እስራኤላዊነትና እውነተኛው፡ የግብፃውያን ክርስቲያናዊ ኦርቶዶክሳዊነት፡ ኹለቱም፡ የእምነት ዓይነቶች፡ በእግዚአብሔር ፈቃድና ዕቅድ፡ በየዘመናቸው፡ በቅደም ተከተል፡ ወደኢትዮጵያ ገብተው፡ ከእነርሱ ከቀደመውና ጥንታዊ ከኾነው፡ ከቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ጋር፡ በተዋሕዶ አንድ ኾነው፡ ለፍጹምነት በቅተዋል።

እውነታው ይህ ኾኖ ሣለ፡ ኢትዮጵያዊነት ብቻ ሳይኾን፡ የእርሱ፡ የማዕዘን ድንጋይና የጒልላት ዕንቍ የኾኑት፡ መልከ ጼዴቅንና ንግሥት ማክዳን የመሰሉት፡ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ጭምር፡ ባለፉትና በዛሬው የኢትዮጵያ ትውልዶች ዘንድ፡ ከገዛ ምድራቸው ተገልለው፡ በእነርሱ ሥፍራ፡ ሓሰተኛው እስራኤላዊነትና ሓሳዊው ኦርቶዶክሳዊነት ብቻ ስለመስፈናቸው፡ ከመጻሕፍታችንና ከመልእክት ጽሑፎቻችን፡ በሚበቃ እንደተገነዘባችሁ እናምናለን። ይህ የጥፋት ድርጊት፡ በክፉቱ ወገኖች፡ እንዴትና ለምን እንደተፈጸመ፡ ነገሩን፡ እስኪ፡ ልብ ብላችሁ ለመመልከትና ለመገምገም ሞክሩ!

አልተቻላቸውም እንጂ፡ ቀደም ብለውና ኋላም፡ ተከታትለው፡ ወደኢትዮጵያ የገቡት፡ በዘመነ ብሉይ፡ "ኦሪታውያን ነን!" የሚሉት፡ የእስራኤል አይሁድና በዘመነ ሓዲስ ደግሞ፡ ከእነርሱ የተከተሉት "ኦርቶዶክሳውያን ነን!" የሚሉት የግብፅ መነኰሳት፡ እግዚአብሔራዊ ሥርዓት የኾነውን፡ እውነተኛውን እስራኤላዊነትና ኦርቶዶክሳዊነት ያዋሓደውን፡ ይህን የቅዱሱን ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ነው፡ ለመለወጥ ብቻ አይደለም፡ ጨርሰው ሊያጠፉት ጭምር የሞከሩት፥ እየሞከሩም ያሉት።

የሙከራቸው ጽናትና ጥልቀት፡ የቱን ያህል ሥር የሰደደ መኾኑ ተረጋግጦ የሚታወቅበት ግልጽ ኹኔታ አለ። ይህም፡ ገና፡ የእነርሱ፡ በሕዝብነት የመኖራቸው እውንታ እንኳ ከመከሠቱና ከመታወቁ በፊት፡ ከአራት እስከአምስት ሺህ ዓመታት አስቀድሞ፡ በገናናነት ሰፍኖ የኖረውን፡ ይህን ኢትዮጵያዊነት፡ ዝክረ ነገሩ እንኳ እንዳይወስሳ ጥብቅ ዕገዳ ለማድረግ መቻላቸው ነው። በዚህ ረገድ፡ ራሱን፡ "ኢትዮጵያዊ ነኝ!" የሚለውን ትውልድ አሳስተው፥ ይህንኑ ሓሰታቸውን እንዲቀበል፥ መቀበል ብቻ ሳይኾን፡ እንዲያምንበትም ማድረጋቸው ነው፡ ማረጋገጫው።

ከዚህ የተነሣ፡ ይህ ትውልድ፡ የሃይማኖት ጒድለትና የምግባር ድክመት እንዲያጠቃው፥ የአምልኮ ተገዢነትና ባርነት እንጂ፡ ከኢትዮጵያዊነት የነጻነት ባሕርያት መካከል፡ አንዱንም እንዳያገኝ ተጨቍኖና ላልተቋረጠ ከባድ ተፅዕኖ ተዳርጎ ኖረ፤ ይህም ኹኔታው፡ እስከዛሬና ዛሬም፡ በይፋ እንደሚታየው፡ አዚም እንደተደረገበት ሰለባ፡ ስለምንነቱና ስለማንነቱ፡ የሚይዘውንና የሚከተለውን አጥቶ፡ ሲናውዝ በመገኘቱ፡ ገመናውን ከሥቶበታል።

## ፩. የአሪታውያንን እስራኤላዊነት፡ በአንደኛ ደረጃ፡ ይመለከቷል።

ኢትዮጵያዊው ትውልድ፡ የአዳምና የሔዋንን ፍጥረት መነሻው አድርጎ፡ የ፯ሺ፭፻፭ (ሰባት ሽህ አምስት መቶ አምስት) ዓመታት፡ የነጻነት ህልውናን የሚያስቆጥረውን፥ በኢትዮጵያዊነቱም የሚያኮራውን፡ ገናና ዝና ትቶ፡ ዘወትር ሲለፍፍ የሚደመጠው፡ የአሪታውያኑ እስራኤሎች የተፅዕኖ ኃይል፡ የኋላ ኋላ፡ ወደኢትዮጵያ ገብቶ መስፈን የጀመረበትን ዜና መዋዕል ነው።

ይኸውም፡ እስራኤላዊው የተፅዕኖ ኃይል፡ ከኢትዮጵያዊቷ ንግሥት ማክዳና ከእስራኤላዊው ንጉሥ ሰሎሞን የተወለደውን፡ የቀዳማዊ ምኒልክን የንግሥና ዘመን መነሻው ያደረገውን፥ አገዛዙንም፡ በዚህ መልክ፡ በራሱ፡ በኢትዮጵያዊው ትውልድ ላይ ሊያሰፍን ያስቻለውን፡ ኢትዮጵያዊዉን የህልውና ዕድሜ፡ በሦስት ሺህ ዓመታት ብቻ ወስኖ፡ ይህን የስሕተት ዘመን ለመመሥረት የተጠቀመበት፡ የሐሰት ይትበሃሉ መኾኑ ይታወቃል።

ኢትዮጵያዊው ትውልድ፡ እስከዛሬና ዛሬም፡ ያለኀፍረትና ያለይሉኝታ፡ መላልሶ የሚናገረውና የሚጽፈው፥ የሚያሠራጨውና የሚያውጀው፡ ይህ አሳፋሪ ይትበሃል፡ በቤተ ሕዝቡ ዘንድ፡ ቋሚ ባህል ኾኖ መቀጠሉ ብቻ ሳይኾን፥ የቤተ መንግሥቱ ሕጋዊ የአዋጅ ቃል፥ የቤተ ክህነቱም ሃይማኖታዊ አቋም ኾኖ፡ የሦስት ሺሆችን ዓመታት ዕድሜን ማስቆጠሩ፡ ይኸው፡ እስካኹን ጸንቶ በቀጠለው፡ የትውልዱ አመራርና አሠራር፡ በጉልህ ይታያል።

ይኹን እንጂ፡ እንኳንስ፡ ኋላ፡ በተከታታይነት ለመጡት፡ ለኪዳነ ኦሪቱና ለክርስትናው የኪዳነ ምሕረት እምነቶች ቀርቶ፡ ለመጀመሪያውና ለጥንታዊው የኪዳነ ልቦናው የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ሃይማኖትም ጭምር፡ ምንጭ በኾነችው፡ በኢትዮጵያ፡ ይኸው ስሑት ይትበሃል፡ ለዚህን ያህል ዘመን፡ እንዲህ ተንሠራፍቶ ለመቀጠል መቻሉ ሳያስደንቅ አልቀረም። ማስደነቁም፡ ያለምክንያት አይደለም፤ ይትበሃሉ፡ የተሳሳተ መኾኑን አረጋግጠው የሚያስረዱ፡ እንደዐለት የጸኑ የምስክር ሓውልቶች እያሉ፡ ሓሰቱ፡ ተጠናክሮ፡ እስከዛሬ መቀጠሉ ነው፤ ከእነዚህ የምስክር ሓውልቶች መካከል፡ ጥቂቶቹ፡ ከዚህ እንደሚከተለው ተጠቅሰው ይገኛሉ፡-

በቅድሚያ፡ የዕብራውያን አባት የኾነውንና ጣዖት አምላኪ የነበረውን አብርሃምን፡ ለኪዳነ ልቦናው የኢትዮጵያዊነት ሃይማኖትና በቅዱሱ ኪዳን አራተኛውን ተራ ለያዘው፡ ለግርዛቱ ቃል ኪዳን ያበቃው፡ ያ፡ ከአዳምና ሔዋን፡ እስከኖኅ የደረሰውን፡ የቅዱሱን ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ሕያው ቅርስ የተረከበው፡ ኢትዮጵያዊው መልከ ጼዴቅ መኾኑ ነው፤ (ዘፍጥ. ፲፬፥ ፲፰-፳። መዝ. ፻፱፥ ፬። የሓዋ. ፰፥ ፳፮-፴፱። ዕብ. ፯፥ ፩-፳፰።)

በመካከሉ፡ እነዚህኑ፡ "የአብርሃም ልጆች ነን!" የሚሉትን ዕብራውያንን፡ ከግብፅ የባርነት አገዛዝ ነጻ አውጥቶ፡ ለኪዳነ ኦሪቱ ሃይማኖትና ለከነዓን ምድረ ርስት ያበቃቸውን፡ ሙሴን፡ እግዚአብሔር፡ አስቀድሞ፡ ወደኢትዮጵያ አምጥቶ፡ ስለቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት እንዲያውቅና እንዲያምን፥ ኢትዮጵያዊቷን ሲጳራንም፡ በሚስትነት እንዲያገባና ከእርሷ ልጆችን እንዲወልድ ካደረገው በኋላ፡ በዚህ የኢትዮጵያዊነት ማንነቱ፡ ወደፈርዖን መላኩ ነው፤ (ዘጸአ. ፪-፫ እና ፲፰፤ ዘኍል. ፲፪።)

በመጨረሻ፡ ከኢትዮጵያዊቷ የአምላክ እናት፡ ከድንግል ማርያም ተወልዶ፡ ፍጥረተ-ዓለሙን ያዳነው፡ ኢትዮጵያዊው ልጇ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ለተመሳሳይ ተልእኮ፡ ከእርሱ እንደቀደሙት፡ እንደመልከ ጼዴቅና እንደሙሴ፡ **"ኢተፈነውኩ ዘእንበለ ኀበ አባግዕ ዘተሓጕላ፡ ዘቤተ እስራኤል!" ማለትም፡ "የእስራኤል ወገን ወደኾኑ የጠፉት በጎች ካልኾነ በቀር፡ ወደሌላ አልተላክሁም!"**፥

ደግሞም፡ **"ወኢትፍትሑ፡ በአድልዎ ለገጽ! አላ፡ ፍትሓ ጽድቅ ፍትሑ!" ማለትም፡ "የእውነት ፍርድ ፍረዱ እንጂ፡ መልክ አይታችሁ አትፍረዱ!"** ብሎ ተናግሮ እያስተማረ፡ በመስቀል ተሠውቶና ሞቶ፡ እነዚህኑ ዕብራውያንን ያዳነው፡ በዚሁ ኢትዮጵያዊነቱና መልኩ መኾኑ ነው። (ማቴ. ፲፫፥ ፳፬። ዮሐ. ፯፥ ፳፬።)

## ፪. <u>በግብፃውያኑ በኩል፡ የመጣውን ኦርቶዶክሳዊነት ደግሞ፡ በኹለተኛ ደረጃ፡ ይመለከቷል።</u>

ፈርዖኖች ይገዟት የነበረችው "ግብፅ"፡ ጥንቱኑም፡ በኢትዮጵያውያን የተመሠረተችና የተዳደረች መኾኗ፡ ይታወቃል። የያዕቆብ ልጆች፡ በባርነት ለሸጡት፡ ለትንሹ ወንድማቸው፡ ለዮሴፍ፡ የቢትወደድነትን ሹመት በማቀዳጀትና ኢትዮጵያዊቷን ልጃቸውን፡ "አስናት"ን ለሚስትነት በመዳር፡ እኒሁ ኢትዮጵያውያን፡ ይህንኑ ዮሴፍን፡ ለከፍተኛ ሥልጣን አብቅተውት፡ በእርሱ አማካይነት፡ በረሀብ ሊያልቁ ቀርበው የነበሩትን፡ አባቱንና ወንድሞቹን፥ በጠቅላላ፡ ቤተ-ዘመዶቹን ኹሉ፡ በክብር ተቀብለው ማስተናገዳቸውም አይዘነጋም፤ "የካም ምድር" በኾነችው ግብፅ።

ይህ ኹሉ ዝና ተደምስሶ፡ በእነዚያ አይሁድ ፈታውራሪነት፡ ቀደም ብሎ እንዲሠረዝ የተደረገውን ኢትዮጵያዊነት፡ "ውሻ በቀደደው፣ ጅብ ይገባል!" እንደሚባለው፡ ወደአምልኮ ጣዖት ተዘፍቀው የኖሩትና ክርስትናን፡ በኢትዮጵያዊው ማርቆስ አማካይነት የተቀበሉት ግብፃውያን ደግሞ፡ ከዕብራውያኑ ፍልሰት፡ ሺ፭፻ ዓመታት በኋላ፡ በ፬ኛው ምእት ዓመተ ምሕረት፡ ወደኢትዮጵያ ገብተው፡ በኢትዮጵያዊነት ላይ የፈጸሙትን ጥቃት፡ ከረዥሙ ባጭሩ፥ ከብዙው፡ በጥቂቱ፡ እንደሚከተለው፡ መመልከት ነው፡-

በቅድሚያ፡ ኢትዮጵያውያንን፡ በዚሁ ዘመን፡ "እኛ ነን ለክርስትና እምነት ያበቃናችሁ!" ብለው፡ ይኸው፡ እስከዛሬ፡ የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን፡ "ኦርቶዶክስ" በሚል አጠራር እንድትታወቅ፥ እርሷም፡ ይህንኑ ስያሜና "የክርስትና እምነትን የተቀበልሁት፡ ከክርስቶስ ልደት በኋላ፡ በ፬ኛው ምእት ዓመት ነው!" የሚለውን መተማመኛዋን፡ በሕግ ጭምር እንድታጸድቅላቸው በማስገደድ፡ ግብፃውያን፡ ቅኝ ገዢነታቸውንና አሳማኝነታቸውን ማረጋገጣቸው፤

በመካከሉ፡ የኢትዮጵያዊነትን ክብር ዝቅ የሚያደርገው፡ "ፍትሓ ነገሥት" የሚለው፡ የሕግ መጽሓፋቸው፡ እንደእግዚአብሔር ቃል ተቆጥሮ፡ ተአማኒነቱና ተፈጻሚነቱ፡ ዛሬ ድረስ፡ በዚችው ቤተ ክርስቲያን ላይ፡ በተፅዕኖ ጸንቶ እንዲቀጥል ማድረጋቸው፤

በመጨረሻ፡ አረንጓዴ፥ ብጫና ቀይ የኾኑትን ዓበይት ኅብረ ቀለማትን በያዘውና በኖኅ ቀስተ ደመና አማካይነት፡ የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ምልክት በኾነው፡ በኢትዮጵያዊው የክርስትና ጥምቀት ማተብ ቦታ፡ ቀይ፥ ነጭና ጥቁር ቀለማትን የያዘውን፡ ያገራቸውን፡ የግብፅ ሰንደቅ ዓላማ የማተብ ክር ተክተው፡ መንፈሳዊ አገዛዛቸውን፡ ያለኅፍረት፡"ኢትዮጵያዊ ነኝ!" በሚለው፡ በዚሁ መከረኛና ጐሥቋላ ትውልድ ላይ ቀጥለውበት መገኘታቸው፡ በማስረጃነት ያህል ይበቃል።

ኢትዮጵያዊው ሃይማኖትና ምግባር፥ ሥርዓቱና ባህሉም፡ ጨርሶ ተወግዶ፡ የአይሁድ እስራኤላዊነትና የግብፅ ኦርቶዶክሳዊነት የሰፈነና የሠለጠነ መኾኑ የሚረጋገጥባቸውን፡ ኹለት ቊም ነገሮችን ማውሳት ይቻላል፤ እነዚህም፦

በአንድ በኩል፡ የኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌና አብርሃም አሥራት ያወጣለት፡ ገናናው ኢትዮጵያዊ መልከ ጼዴቅ ሲኾን፥

በሌላ በኩል ደግሞ፡ ለድንግል ማርያም ምሳሌዋ የኾነችው፥ ለታቦተ ጽዮንና ለዳዊት የቃል ኪዳን ዘር ወደኢትዮጵያ መምጣት፡ ምክንያት የኾነችው፡ ስመ ጥሩዪቷ ንግሥት ማክዳ ናት።

የእኒህ፡ የኹለቱም ስም አጠራር፡ በዚችው፡ በኢትዮጵያ፡ የግብፅ ኦርቶዶክስ ቅርንጫፍ በኾነችው ቤተ ክርስቲያን ውስጥ፡ እንኳንስ ለቅድስና የሚያበቃ ክብር ሊሰጣቸው ይቅርና፡ ለዝክረ ነገር እንኳ፡ ስማቸው፡ በጸሎት ላይ እንዳይነሣ በመደረጉ ይረጋገጣል።

እንግዴህ፡ ይህ ትውልድ፡ ራሱ፡ "አውቄዋለሁ! ተምሬዋለሁ!" ብሎ፡ ለሌላ የሚያስተምረውና የሚሰብከው፥ የሚያራምደውና ሽንጡን ገትሮ የሚከራከረውም፡ <u>እግዚአብሔራዊና ቀዳማዊ ስለኾነው፡ ስለዚሁ፡ ስለራሱ ኢትዮጵያዊነት ሳይኾን፡</u> ከዚህ በላይ እንደታተተው፡ ስለኋላ መጦቹ፡ ስለአሪታውያኑ አይሁድ እስራኤላዊነትና ስለባለክርስትናዎቹ ግብፃውያን ኦርቶዶክስነት ብቻ ኾኖ በመገኘቱ፡ ግብሩ መስክሮበታል።

የዛሬዎቹ፡ እውነተኞቹ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ ይህን ሓሳዊ ባህልና ግብር አይቀበሉም፤ አማናዊው የእግዚአብሔር ሥራና ሥርዓት የኾነውን፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነትን፡ የቀደሙት ቅዱሳንና ቅዱሳት ወላጆቻቸው፡ በጥንተ ተፈጥሮው፡ አጽንተውትና ጠብቀውት እንደኖሩት ኹሉ፡ እነርሱም፡ ህልውናውን፡ በዚሁ ጽናትና ጥበቃ፡ በእየራሳቸው ሕይወት እየኖሩትና እየጠበቁት፥ ስለእርሱ የሚነገረውን የምሥራች ዜናና ጥሪም፡ ለፍጥረተ-ዓለሙ ኹሉ እያስሰሙና እያቀረቡ፡ እነሆ፡ የሓዋርያነት አገልግሎታቸውን በመቀጠል ላይ ይገኛሉ።

የምሥራቹን ዜናና ጥሪ ሰምቶና ተቀብሎ፡ የሚመጣውንና በንስሓ የሚመለሰውንም ኹሉ፡ ይቀበላሉ፤ የሚስተካከለውን ያስተካክላሉ።

<u>ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ የተልእኮ ዓላማዋና ተግባሯ፡ እንግዴህ፡ ይኼ ነው!</u>

ይህ ኹሉ እውነታ ተገልጾ፡ በገሃድ እየታየና በይፋ እየተናገረ፡ ዛሬ፡ እርሷን፡ "ኢትዮጵያ" በሚለው ስሟ እየጠሩ፡ እየራሳቸውንም፡ ባገር ውስጥና በውጭ አህጉር፡ በቤተ ሕዝብነት፥ በቤተ ምልክናነትና በቤተ ክህነትነት፡ ከፋፍለውና ለያይተው በሚጠሩበት ስሞቻቸው የሚገኙበትና የሚመሩበት፥ የሚተዳደሩበትና የሚሠሩበት አቋማቸው፡ እግዚአብሔራዊውን ሥርዓት፡ ፈጽሞ የሚፃረር ኾኗል።

"አገልጋዮቿ ነን!" በሚሉ፡ ልጆቿ ጥፋት ምክንያት፡ ዐልፎ ዐልፎ፡ በየዘመናቱ ቢማስንም እንኳ፡ እውነተኛ ንስሓን ባስከተለ ተገቢ ቅጣት እየተስተካከለ፡ እስከዛሬ፡ የቆየው፡ እግዚአብሔራዊው ሥርዓት፡ አማናዊቱ ኢትዮጵያ፡ ከተመሠረተችበትና ከተቋቋመችበት የፍጥረት ዘመን ጀምሮ፡ ለ፯ሺ፭፻፭ ዓመታት ጸንቶ የቀጠለው፡ ቅዱሱ ኪዳን ነው።

ለዚህ ኹሉ፡ እግዚአብሔራዊ ቅርስና ውርስ፡ ባለቤቶችና ባለአደራዎች ሊኾኑ የሚገባቸው፡ የዛሬው የኢትዮጵያ ትውልድ ቤተ ሕዝብ፥ ቤተ ምልክናና ቤተ ክህነት፡ የቀደሙት ደጋጎች ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ወላጆቻቸው፡ ከፈጣሪያቸው፡ ከእግዚአብሔር ጋር ተካይደው፡ በጽኑ ጠብቀውት ከኖሩት፡ ከዚህ፡ ከቅዱሱ ኪዳን፡ እንዲህ፡ ኹሉም፡ በመስማማትና በመተባበር፡ አንድ ኾነው፡ በግልጽ ክህደት፥ በይፋ ዓመፅና በገሃድ አመንዝራነት፡ እየራሳቸውን አግልለዋል።

በዚህ ታላቅ ኃጢአታቸው ምክንያት፡ በመለኮት ውግዘት የተለዩ መኾናቸውን በመግለጽ፡ በንስሓ ይመለሱ ዘንድ፡ ይህች፡ ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ የምሥራቹን ዜና፡ ለእነርሱና ለዓለሙ ኹሉ በማስተላለፏ፡ መልእክቷን ተቀብለውና ሰምተው፡ በመፈጸም ፋንታ፡ በእርሷ ላይ የሚያካኺዱት የተቃውሞ ዘመቻ፡ ምን ዓይነት የተራቀቀና የቱን ያህል ያየለ መኾኑን፡ አስተዋይ ተመልካች የኾነ ሰብአዊ ፍጡር ኹሉ፡ በቀላሉ የሚያውቀው ነው።

ይህም ኹኔታ፡ ለእርሱ፡ ለእግዚአብሔር፥ ለቅድስት እናቱም፡ ክብርና ምስጋና ይድረሳቸውና፡ የአይሁድ ቤተ ሕዝብና ቤተ ክህነት፥ በዚያን ጊዜ፡ የቤተ ምልክናው አገዛዝ ባለቤት ከነበረው፡ ከሮማው የቄሣር መንግሥት ጋር በመተባበር፡ በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስና በእመቤታችን ድንግል ማርያም ላይ ይፈጽሙት የነበረውን ተቃውሞ መስሎ ስለተገኘ፡ በምንም መልኩ ሊያስደንቅ፥ ሊያስገርምም አይችልም፤ የሚጠበቅ፥ ሊኾንም የተወሰነ ነውና።

እንዲያውም፡ ለእኛ፡ ለኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት አገልጋዮች፡ ማንነታችንንና የማን ወገን መኾናችንን፡ አረጋግጦ ስለሚያሳውቅልን፡ በበለጠ የሚያስደስተንና የሚያጠናክረን፥ ለምሥራቹ ክብር የሚያበቃንም ነው እንጂ።

ጌታችን፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ **"ወበዓለምሰ፡ ሕማመ ትረክቡ! ወባሕቱ፡ ጽንዑ! እስመ አነ ሞእክዎ ለዓለም።" ማለትም፡ "በዓለም ሣላችሁ፡ መከራ ይደርስባችኋል፤ ግን፡ አይዟችሁ! እኔ፡ ዓለሙን፡ ድል ነሥቼዋለሁ። እናንተም ታሸንፉታላችሁና፡ ጽኑ!"** ሲል እንደተናገረው። (ዮሐ. ፲፮፥ ፴፫።)

## ኢትዮጵያዊው <u>ምንነታችሁ፡</u> ለብቻው ምንድን ነው?

ይህ፡ የአንተ እና የአንቺ <u>"ምንነት"</u>፡ ለብቻው ሲገለጽ፡ ኹሉን በፈጠረና የኹሉ ባለቤት በኾነው ፈጣሪ ጥበብና እጅ፡ የተፈጠራችሁበት <u>"ፍጡርነታችሁ"</u> ኾኖ ይገኛል። በዚህ ፍጡርነታችሁ፡ ሰውነታችሁን፡ የእርሱ ማደሪያ፡ ማለትም፡ "**ቤተ መቅደስ**" አድርጋችሁ፣ እርሱው ፈጣሪያችሁ፡ ጥንቱኑ፡ ምንና እንዴት ኾናችሁ እንድትገኙ ለሚፈቅደው የህልውና ዓይነት፡ እየራሳችሁን ማብቃት እንዳለባችሁ፡ ይኸው የምንነታችሁ ተፈጥሮ፡ በየአፍታው ያስገነዝባችኋል።

ይህ የምንነት እውነታ፡ እንደምን በተግባር ላይ ውሎ፡ ለፍሬ ሊበቃ እንደቻለ፡ ሰውነታቸውን፡ ለእግዚአብሔር ማደርያነት ሰጥተውና አካኼዳቸውን ከእርሱ ጋር አድርገው የኖሩትን፡ አቤልን፥ ሄኖክን፥ ኖኅንና ኀይከልን፥ መልከ-ጼዴቅንና ሳሌምን፥ አብርሃምንና ሣራን፥ ኬጡራን፥ ዮቶርን፥ ሙሴንና ሲጳራን፥ ሳሙኤልን፥ ኤልያስን፥ ዳዊትን፥ ንግሥት ማክዳን፥ ዘካርያስንና ኤልሣቤጥን፥ መጥምቁ ዮሐንስን፥ ኢያቄምንና ሐናን፥ ድንግል ማርያምን የመሰሉትን እውነተኞች ሰዎች፡ ለአብነት በመጥቀስ፡ ምሳሌነታቸው፡ በገሃድ እንዲያስረዳ ማድረግ ይቻላል።

ከዚህ ኹሉ በላይ ግን፡ ራሱ እግዚአብሔር ወልድ፡ ሰው ኾኖና "ኢየሱስ ክርስቶስ" ተብሎ፡ በዚህ ዓለም፥ በምድር ላይ በፈጸማቸው ተአምራቱና መልካም ምግባራቱ፡ ይህ እውነታ፡ በተትረፈረፈ መጠን ተረጋግጧል። ለማስረጃነት ያህል፡ መምህራችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ይህን ርእስ በሚመለከት ከተናገራቸው፡ ከቅዱስ ቃሎቹ መካከል፡ ከዚህ የሚከተሉትን፡ ጥቂቶቹን እንጠቅሳለን፡-

፩ኛ፡ ሰዎች፡ እርሱን፡ ማን እንደሚሉት ለማወቅ፡ ደቀ መዛሙርቱን ጠይቋቸው፡ ሰዎችማ፡ ከቀደሙት ነቢያት፡ እንደአንዱ እንደሚቈጥሩት ከገለጹለት በኋላ፡ "*አንትሙሰ*ኬ፡ *መነ ትብሉኒ ከዊነ?*" ማለትም፡ "*ታዲያ! እናንተሳ፡ እኔን፡ 'ማን ነው?' ትሉኛላችሁ?*" ብሎ ላቀረበላቸው ጥያቄ፥

ሊቀ ሓዋርያት ቅዱስ ጴጥሮስ፡ "*አንተ ውእቱ፡ ክርስቶስ ወልደ እግዚአብሔር!*" ማለትም፡ "*አንተ፡ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ ነህ!*" ሲል፡ ለሰጠው ምላሽ፡ ጌታችን፡ የተናገረው ቃሉ፡ እንዲህ በማለት ይመሰክራል፡-

"*ብፁዕ አንተ፡ ስምዖን ወልደ ዮና! እስመ ኢከሠተ ለከ፡ ዘሥጋ ወደም፤ አላ፡ አቡየ ዘበሰማያት። ወአንሰ እብለከ፡ ከመ አንተ ኰኵሕ፤ ወዲበ ዛቲ ኰኵሕ፡ አሓንፃ ለቤተ ክርስቲያንየ። ወአናቅጸ ሲኦል ኢይሔይልዋ። ወእሁበከ መራኁተ መንግሥተ ሰማያት። ወዘአሰርከ በምድር፡ ይከውን እሱረ በሰማያት፤ ወዘፈታሕከ በምድር፡ይከውን ፍቱሓ በሰማያት።*"

ማለትም፡ "*የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ! ይህን እውነት የገለጸልህ፡ የሰማዩ አባቴ እንጂ፡ ሥጋዊውና ደማዊው ሰውነትህ አይደለም። እኔም፡ እልሃለሁ፡- 'አንተ፡ ዓለት ነህ፤ በዚችም ዓለት ላይ፡ ቤተ ክርስቲያኔን እሠራታለሁ፤ የሲኦል ደጆችም አይችሏትም። የመንግሥተ ሰማያትንም መክፈቻዎች እሰጥሃለሁ። በምድር ያሰርኸው፡ በሰማያት፡ የታሰረ ይኾናል፤ በምድር የፈታኸውም፡ በሰማያት፡ የተፈታ ይኾናል።'*" (ማቴ. ፲፮፥ ፲፯-፲፱።)

እንግዲህ፡ ቅዱስ ጴጥሮስ የተናገራቸው፡ የሃይማኖት ማረጋገጫ ሕያዋን ቃላት፡ በእግዚአብሔር መልክ በተፈጠረ፡ በማንኛውም፡ ወንድ ኾነ ሴት ምእመን/ምእመኒት፡ የልብ ጽላት ላይ፡ በመንፈስ ቅዱስ ጣቶች፡ የተጻፉ ናቸው።

ይህ ምእመን / ይህች ምእመኒት፡ እኒያን ሕያዋን ቃላት፡ እያንዳንዳቸው፡ ከእውነተኛ መንፈሳዊ ልቦናቸው አፍልቀው፡ በአንደበታቸው ሲያስሰሙና በይፋ ሲመሰክሩ፡ ዘለዓለማዊው መምህራችን፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ለቅዱስ ጴጥሮስ የተናገረው ይህ የአዋጅ ቃል፡ ለእርሱ፥ ወይም፡ ለእርሷ፡ የሚጸና ኾኖ፡ ያን፡ መለኮታዊ የሹመት ሥልጣን ይቀዳጃል፥ ትቀዳጃለች።

በዚህ መለኮታዊ ቃል መሠረት፡ አንተ እና አንቺ፡ "*አንተ ውእቱ፡ ክርስቶስ ወልደ እግዚአብሔር!*" ማለትም፡ "*አንተ፡ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ ነህ!*" ብላችሁ፡ በልባችሁ ያለውን እምነታችሁን፡ በአንደበታችሁ በመናገር፡ በእውነት በምታረጋግጡበት ጊዜ፡ እናንተም፡ እየራሳችሁ፡ አንተም፥ አንቺም፡ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደሱ፥ ቤተ ክርስቲያኑ ትኾናላችሁ፤ ለእርሱ፡ ለቅዱስ ጴጥሮስ የተሰጠው የክህነት ሥልጣን ጭምር፡ የአንተም፥ የአንቺም ይኾናል።

"የአንተም፥ የአንቺም ይኾናል!" ሲባል፡ እንግዳ ነገር አይኹንባችሁ! ከጥንት፥ ከመሠረቱ፡ ጸንቶ፡ ሲሠራበት እንደተኖረው፡ እንደቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ሥርዓት፡ በቀድሞው የብሉይ ኪዳኑ ዘመን የነበሩትን፡ ገናናዪቱን ማክዳንና ልጇን ቀዳማዊ ምኒልክን፥ በኋለኛውም የአዲስ ኪዳኑ ዘመን የነበሩትን፡ ስመ ጥሩዪቱን ሕንደኬንና ካሌብን የመሰሉት ኹሉ፡ እነማን ይመስሏችኋል?

እንደአንቺና እንደአንተ፡ ዕሩቅ ብእሲዎች፡ ማለትም፡ ተራ ሰዎች ናቸው እኮ!? በሥይምተ እግዚአብሔር ንግሥትነትና በሥዩመ እግዚአብሔር አጼነት፡ የቤተ ሕዝቡ፥ የቤተ ምልክናውና የቤተ ክህነቱ የበላይ ቊንጮዎች፥ ጉልላቶች፥ ዘውዶች ኾነው እንዲያገለግሉ ያሳጫቸውና ያስመረጣቸው፡ ምንና ማን መሰላችሁ? እየራሳቸውን፡ <u>ለቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት አብቅተው በመገኘታቸው፥</u> ይህንኑም እግዚአብሔር ስላወቀ፡ ነው እኮ!?

እናንተም፡ እንዲሁ፡ እንደነርሱ፡ <u>እየራሳችሁን፡ ለዚሁ፡ ለቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት አብቅታችሁ በምትገኙበት ጊዜ፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ዘንድ፡ ለንግሥትነትና ለአጼነት የበቃችሁ ኾናችሁ እንደምትገኙ አታውቁምን?</u> መብቃት ብቻ አይደለም፤ መኾናችሁን ጭምር፡ አታቁምን? ያላወቃችሁ ከኾናችሁ፡ እንግዴህ ወዲህ፡ እወቁት!

ለየዘመኑ፡ የዘውዱና የዙፋኑ፥ የበትረ መንግሥቱም ባለአደራነት፡ በመንፈስ ቅዱስ፡ ከቅድስት ድንግል ማርያምና ከልጇ ከኢየሱስ ክርስቶስ ታጭተውና ተመርጠው የሚቀቡትና የሚሾሙት ንግሥትና አጼ እኮ፡ ከእነዚሁና እነርሱን ከመሰሉት፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት መካከል ነው እኮ!

በኢትዮጵያውያንና በኢትዮጵያውያት ዘንድ የኖረው ሃይማኖታዊው የቅዱሱ ኪዳን ባህልና ሥርዓት፡ በተለይ፡ ኢትዮጵያዊት ሴትን በሚመለከት፡ መብቷና ሥልጣኗ፡ በዚህ የንግሥትነት ክብርና ማዕርግ ብቻ የተወሰነ አልነበረም፤ ማለትም፡ ክብሯና ማዕርጓ፡ በቤተ ሕዝቡና በቤተ ምልክናው ብቻ ሳይኾን፡ በቤተ ክህነቱም ላይ ጭምር፡ በነበራት የበላይነት መብቷና ሥልጣኗ ብቻ የተወሰነ አልነበረም።

ነገር ግን፡ **"ናሁ፡ ድንግል ትፀንስ፤ ወትወልድ ወልደ፤ ወትሰምዮ ስሞ አማኑኤል!"** ማለትም፡ **"ድንግል ትፀንሳለች፤ ወንድ ልጅንም ትወልዳለች፤ ስሙንም አማኑኤል ትለዋለች!"** በሚለው የትንቢት ቃል መሠረት፡ ለዚያ የንግሥትነት ክብርና ማዕርግ የምትበቃው ኢትዮጵያዊት ሴት፡ በድንግልናዋ ጸንታ እንድትገኝ ይደረግ የነበረው፡ **"የእግዚአብሔርን ልጅ፡ በድንግልና የምትወልድ እርሷ ናት!"** ተብሎ ይታመን ስለነበረ መኾኑ፡ እዚህ ላይ በአጽንዖት ሊጠቀስ ይገባዋል። (ኢሳ. ፯፥ ፲፬። ማቴ. ፩፥ ፳፫።)

ይህም የትንቢት ቃል፡ በቅድሚያ፡ ኢየሱስ ክርስቶስን ያፈራውን፡ የቃል ኪዳኑን ዘር፡ ከዳዊት ልጅ፡ ከእስራኤሉ ንጉሥ፡ ከሰሎሞን፡ በድንግልና ወደኢትዮጵያ ባመጣችው፡ በኢትዮጵያዊቷ ንግሥት ማክዳ፥ ቀጥሎም፡ በመጨረሻው የሕይወት ዘመን፡ ከዚያ የቃል ኪዳን ዘር ተገኝታ፡ እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ ክርስቶስን፡ በድንግልና በወለደችው፡ በኢትዮጵያዊቷ ቅድስት ድንግል ማርያም፡ ተረጋግጦ እውን ኾኗል፤ ተፈጽሟልም።

ይህን የእግዚአብሔር እውነት፡ እስካኹን፡ ወንዶችም፥ ሴቶችም፡ አላወቃችሁ እንደኾነ፡ እንግዴህ ወዲህ አውቃችሁትና አምናችሁበት፡ ደስ ብሏችሁና እያመሰገናችሁ፡ በሕይወት ልትኖሩት ያስፈልጋችኋል፤ ይገባችኋልም።

እዩት! አስተውላችሁ ተመልከቱት! እንዲህ ያለው ክብርና ሥልጣን፡ ከቸሩ ፈጣሪያችሁ፡ ለአንተም፥ ለአንቺም ተሰጥቷችሁ ሣለ፡ እስከዛሬና ዛሬም፡ ሳታውቁትና ሳትጠቀሙበት እየኖራችሁ ነው ያላችሁት።

ይህ ብቻ አይደለም፤ ከዚህ የተነሣ፡ <u>የእናንተ ሰውነት፡ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ እንደመኾኑ መጠን፡ ይህ ቤተ መቅደስ የሚያድርበት፥ የሚኖርበትም ቤታችሁ ደግሞ፡ ቤተ ክርስቲያን ነው፤</u> በዚህ መኖርያ ቤታችሁ ውስጥ ሊካኼድና ሊፈጸም የሚገባው፡ የሰይጣን የኾኑት፡ ክፋትና ሓሰት፥ ኃጢአትና አምልኮ ባዕድ ሳይኾኑ፡ የእግዚአብሔር የኾኑት፡ ደግነትና እውነት፥ በጎው ምግባርና አምልኮተ እግዚአብሔር ብቻ ናቸው።

፪ኛ፡ "ኵሉኬ ዘይሰምዕ ዘንተ ቃልየ ዘይገብሮ፡ ይመስል፡ ብእሴ ጠቢበ፡ ዘሓነጸ ቤቶ፡ ዲበ ኰኵሕ። ዘንሙ ዝናማት፤ ወውኅዙ ወኀይዝት፤ ወነፍሑ ነፋሳት፤ ወገፍዕዎ ለውእቱ ቤት፤ ወኢወድቀ፤ እስመ ዲበ ኰኵሕ ተሣረረ።

"ወኵሉ ዘይሰምዕ ዘንተ ቃልየ፡ ወኢይገብሮ፡ ይመስል፡ ብእሴ ዓብደ፡ ዘሓነጸ ቤቶ፡ ዲበ ኆፃ። ዘንሙ ዝናማት፤ ወውኅዙ ወኀይዝት፤ ወነፍሑ ነፋሳት፤ ወገፍዕዎ ለውእቱ ቤት፤ ወወድቀ፤ ወኮነ ድቀቱ ዓቢየ።"

ማለትም፡ "ይህን ቃሌን ሰምቶ፡ የሚያደርገው ኹሉ፡ ቤቱን፡ በዓለት ላይ ያነጸ፡ ብልህ ሰውን ይመስላል። ዝናብም ወረደ፤ ጐርፍም መጣ፤ ነፋስም ነፈሰ፤ ያንም ቤት ገፋው! ነገር ግን፡ ያ ቤት፡ በዓለት ላይ ስለተመሠረተ፡ አልወደቀም።

" ይህን ቃሌን ሰምቶ የማያደርገው ኹሉ፡ ቤቱን በአሸዋ ላይ የሠራ፡ ሰነፍ ሰውን ይመስላል። ዝናብም ወረደ፤ ጐርፍም መጣ፤ ነፋስም ነፈሰ፤ ያንም ቤት መታው! ወደቀም። አወዳደቁም፡ ታላቅ ኾነ! (ማቴ. ፯፥ ፳፬-፳፯።)

እንግዴህ፡ በጌታችን፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ቃል፡ ያ፡ "ቤት" የተባለው ምሳሌ፡ የእያንዳንዳችን ሰውነት ነው።

ይህን ሰውነት፡ በዓለት ላይ እንደተመሠረተው ቤት፡ በረቂቁም ኾነ በግዙፉ፥ በሥጋዊዉም ኾነ በመንፈሳዊው፡ በማንኛውም ዓይነት የፈተና እሳትና የመከራ ማዕበል ሳይሸነፍ፡ በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ሃይማኖቱና ምግባሩ፥ ሥርዓቱና አቋሙ ጸንቶ እንዲገኝ ማድረግ፡ ራስን፡ ለዚያ፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ለሐዋርያው ለቅዱስ ጴጥሮስ ላቀዳጀው ቤተ ክርስቲያንነት ማብቃት ነው።

፫ኛ፡- "ወይነብሩ ሰብእ ብዙኃን ምስሌሁ፤ ወይቤልዎ፡ 'ነዮሙ፡ እምከኒ፥ ወአኃዊከኒ አፍአ፤ ይቀውሙ፤ ወየኀሥሡከ!' ወአውሥአ፤ ወይቤሎሙ፤ 'መኑ ይእቲ እምየ? ወእለ መኑ እሙንቱ አኀውየ?' ወነጸሮሙ ለእለ ይነብሩ ዐውዶ፤ ወይቤ፡ 'ነዮሙ፡ እምየኒ፥ ወአኀውየኒ፤ እስመ ኵሉ ዘይገብር ፈቃዶ ለእግዚአብሔር፡ ውእቱ፡ እኁየኒ፥ ወእኅትየኒ፥ ወእምየኒ።'"

ማለትም፡ "ብዙዎች ሰዎች ዐብረውት ተቀምጠው ነበሩና፡ 'እናትህና ወንድሞችህ፡ እነሆ፡ በውጭ ቆመዋል፤ አንተንም ይፈልጉሃል!' አሉት፤ እርሱም መልሶ፡ እንዲህ አላቸው፡- 'እናቴ ማን ናት? ወንድሞቼስ፡ እነማን ናቸው?' በዙርያው ያሉትንም ተመልክቶ፡ 'እናቴም፥ ወንድሞቼም፡ እነዚህ ናቸው፤ የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚያደርግ ኹሉ፡ እርሱ፡ ወንድሜ፥ እህቴም፥ እናቴም ነው!' አለ።" (ማር. ፫፥ ፴፩-፴፭።)

እዩት! እግዚአብሔር፡ እያንዳንዳችን፡ በእርሱ ዘንድ፡ያለንን፡ <u>የምንነት ደረጃ፡</u> ከምን ዓይነቱ የብቅዓት ማዕርግ እንዳደረሰው ተመልከቱት! ትልልቆችን፡ እንደእናቱ ቅድስት ድንግል ማርያም፥ ወንዶችን፡ ወንድሞቹ፥ ሴቶቹንም፡ እኅቶቹ አደረገ። ይህን አምላካዊ እውነታ፡ አውቀን እንድንቀበለውና አምነንበት፡ ሕይወት አድርገን እንድንኖረው የሚያስችለን፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነታችን ነው።

ስለዚህ፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ የእውቀትና የንስሓ ሥርዓት፡ ይህን የመሰለውን ማንነታችንን ልናድሰው፥ ልናጸድቀውም ይገባናል።

## ኢትዮጵያዊው <u>ማንነታችሁ፡</u> ለብቻው ምንድን ነው?

<u>"ማንነታችሁ"</u> ደግሞ፡ ለብቻው ሲገለጽ፡ ደጉንና ክፉውን፡ ለይታችሁ አውቃችሁ፡ ከኹለቱ፡ አንዱን፡ ለመምረጥ፥ ለመወሰንና ለማድረግ የምትችሉበት፡ በእግዚአብሔር መልክ የተፈጠራችሁበትና የእርሱ ልጆች፥ አገልጋዮችና ነጋሢዎች ለመኾን የበቃችሁበት፡ በሥጋ፥ በነፍስና በመንፈስ የተዋሕዶ አካላትና ባሕርያት አንድ የኾናችሁበት "ሰብአዊነታችሁ" ነው።

ስለዚሁ ማንነታችሁ፡ ኹለት ታላላቅ ቍም-ነገሮችን እናነሣለን፤ እነዚህም፡- ፩ኛው. በእግዚአብሔር መልክ የመፈጠራችሁና እርሱን የመኾናችሁ፡ ትንግርታዊው ምሥጢር ነው። ያም እውነታ፡ "እግዚአብሔር፡ አስቀድሞ፡ 'አዳም!' የተባለውን፡ ሰው፡ <u>እግዚአብሔርን አስመስሎ፥</u> ወንድ እና 'ሔዋን!' የተባለች ሴት አድርጎም፡ ፈጠረው፤

ቀጥሎ፡ ይኸው ሰብአዊ ፍጡር፡ በፈጣሪው መልክ ከተፈጠረበት፡ ከዚህ ባሕርዩ ባመነጨው፡ በራሱ ፍላጎትና ፈቃድ፡ የእውቀትን ዛፍ ፍሬ በበላ ጊዜ፡ ፍጹም እንደእግዚአብሔር ኾነ!

በመጨረሻም፡ እግዚአብሔር ቃል፡ 'ኹለተኛው አዳም!' ተብሎ፡ 'ኹለተኛዋ ሔዋን!' ከተባለችውና የሕይወት ዛፍ ከኾነችው፡ ከድንግል ማርያም ተወልዶ፡ የዚችው የሕይወት ዛፍ ፍሬ የኾነውንና መለኮት የተዋሓደውን የሰውነቱን፡ ቅዱስ ሥጋ በመብላትና ክቡር ደሙን በመጠጣት፡ ፍጡሩ ሰው፡ ከወደቀበት፡ ከክፋት፥ ከኃጢኣትና ከሞት አዘቅት ወጥቶ፡ ለአንዴና ለዘለዓለም ዳነ!" የሚለው ምሥራች ነው።

፪ኛው፡ ይህን ትንግርታዊ ምሥጢር አውቃችሁትና አምናችሁበት፡ በሕይወታዊነት እንድትኖሩት የሚያስችላችሁ፡ መለኮታዊ ጸጋ ነው። ያም፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነታችሁ ነው።

የእግዚአብሔርና ዘለዓለማዊ የኾነውን፡ ይህን፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነታችሁን፡ ከሌሎቹ የማንነት መለያዎች ይልቅ፡ ልዩ የሚያደርገው፡ የራሱ ባሕርይ አለው፤ ይኸውም፡ ይኸው የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነታችሁ፡ አንድን ሰብአዊ ፍጡር፡ ለእነዚህ ኹለት ታላላቅ ቍም-ነገሮች፡ ባለቤትነትና ተጠቃሚነት፡ የማብቃት ኃይሉ ነው። በሌላ አገላለጽ፡ "ይህን የማንነታችሁን ፍጹም እውቀት የምታገኙበት፥ እውቀቱን ካገኛችሁም በኋላ፡ ለመልካም ፍሬ አብቅታችሁት፡ እየራሳችሁ፡ በሕይወት ልትኖሩት የምትችሉበት ረቂቅና ፍቱን ኃይል የሚመነጨው፡ ከዚሁ፡ ከቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነታችሁ፡ ነው!" ማለት ይኾናል።

እንዲህ ከኾነ፡ በቅድሚያ ሊቀርብና ሊመለስ የሚገባው ጥያቄ፡ በእርግጥ፡ ይህን "ኢትዮጵያዊነታችሁን፡ በትክክል አውቃችሁታልወይ?" የሚለው ይኾናል። አውቃችሁት ከኾነ፡ መልካም ነው።

ነገር ግን፡ በእናንተ ዘንድ፡ በየግልም ኾነ በየጋራችሁ፡ እየኾነና እየተደረገ የሚታየው እውነታ፡ ይህ፡ መልካሙ የእውቀት ገጽታ አይደለም። ተቃራኒው፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነታችሁን፡ ፈጽሞ፡ አለማወቃችሁ እንጂ፤ "አውቀነዋል!" ልትሉም አለመቻላችሁ ነው።

ምክንያቱም፡ የሕይወታችሁ መነሻ፡ በአካኼዱ መልክና ይዘት በኩል ዐልፎ፥ እስከመድረሻው ባለው፡ በመጨረሻው ውጤቱ ሲታይ፡ ተጨባጩ ፍሬ፡ ስለቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነታችሁ፡ ፈጽሞ ያለማወቃችሁ ነው።

አውቃችሁትማ ቢኾን ኖሮ፡ የእናንተ ብቻ ሳይኾን፡ ከጥቂቶች በቀር፡ እጅግ ያብዛኛው የሰው ወገን ኹሉ ኑሮ፡ እንዲህ፡ በክፋት እየተጀመረ፥ ቀጥሎ፡ በሓሰት ኃጢኣት እየተለወሰ ከቆየ በኋላ፡ የሙስናው ጽዋ ሲሞላ፡ ያ ሰውነትና ኑሮው፡ በሕመምና በመከራ ይሠቃይና፡ ፍጻሜው፡ ሞትና መቃብር፥ መበስበስም ባልኾነ ነበር።

ነገር ግን፡ ያ፡ በፍጹም ንጽሓ ባሕርይና በእግዚአብሔራዊው መልካምነት፡ ወደዚህ ዓለም የመጣው ሰው፡ ባለመታደል፡ ሳያስበውና ሳያውቀው ይያዝና፡ መጨረሻው፡ ጽኑ በኾነ ብልሹነት፡ ከተሠቃየበት ዓለም፡ እያወቀው ተሰናብቶ፡ ይኼዳል።

እናንተም፡ እየራሳችሁን፡ ለቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ሳታበቁ ከቀራችሁ፡ ይህ ጽዋ፡ ያለጥርጥር፡ የእናንተም ኾኖ፡ ሳትወድዱ በግድ ጨልጣችሁ ትጠጡት ዘንድ፡ ሊቀርብላችሁ፡ ተዘጋጅቶ ይጠብቃችኋል።

## መድረሱ የማይቀረው ዕዳ።

ይህ አሳዛኝ ኹኔታ፡ ለምን፡ በእያንዳንዱ ሰብአዊ ፍጡር ላይ መድረሱ የማይቀር ዕዳ ኾነ? እስኪ፡ ምክንያቱን፡ እንመርምር!

መሠረታዊው ምክንያት፡ ኢትዮጵያዊ ማንነትን አለማወቅ ኾኖ ይገኛል። የዚህ እውነታ፡ በሌላ አገላለጽ ሲቀርብ፡ "በዚህ አንጻር፡ ኢትዮጵያዊ ማንነትን ለማወቅ ከተቻለ፡ አኹን፡ በአካለ ሥጋ በምንኖርበት፡ በዚህ ዓለም ኾነ፡ በሚመጣው ዓለም፡ ሰውን ኹሉ፥ እናንተን ጭምር፡ እያንዳንዱን ሰብአዊ ፍጡር፡ ከሚጠብቀውና ከማይቀረው፡ ከዚያ፡ ከክፋትና ከኃጢአት፥ ከሞትና ከጥፋት የዘለዓለም ፍዳ፡ ራስን ማዳን ይቻላል!" ማለት ይኾናል።

እንግዴህ፡ እውነታው፡ ይህ ከኾነ፡ በዚህ ዓለም ኾነ፡ በሚመጣው ዓለም፡ መጥፋትን ሳይኾን፡ መዳንን፥ ይህም ማለት፡ አሳዛኙን ክፉ ሞት ሳይኾን፡ አስደሳቹን፡ መልካም ሕይወት ለማትረፍ፡ በእውነትና በእርግጥ የምትፈልጉ ከኾናችሁ፡ ይህን፡ የቅዱሱን ኪዳን ኢትዮጵያዊ ማንነታችሁን ለማወቅ ስትሉ፡ የማታደርጉትና የማትኾኑት፥ የማትከፍሉትም ዋጋ፡ "ጨርሶ አይኖርም!" ቢባል ተገቢ ይኾናል። በዚህ መመሪያ ቃል መሠረት፡ ወደቁም ነገሩ እንገባለን።

## እግዚአብሔርን መምሰል።

ሰው የተፈጠረው፡ መልካምንና እውነትን፥ ሕይወትንም መርጦ፡ እግዚአብሔርን መስሎ፡ ለዘለዓለም እንዲኖር ነው፤ "የእግዚአብሔር ልጆች" የሚያስብለው፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነትም፡ ይህ ነው።

ነገር ግን፡ ይኸው ሰው፡ ከዚህ የተለየውንና ተቃራኒውን፡ ክፋትንና ሓሰትን፥ ሞትንም በሚመርጥበት ጊዜ፡ ራሱ፡ "ሰይጣን" ይኾናል፤ "የሰው ልጆች" የሚያስሰኘው ጎራ፡ ከሌሎቹ ሃይማኖቶች ጋር፡ ሓሳውያኑን የአይሁድ እስራኤላዊነትንና የግብፅ ኦርቶዶክሳዊነትን የሚያጠቃልል ኾኖ፡ ይህን የመሰለው ሰው የሚገኝበት ወገን ነው።

እግዚአብሔር፡ እናንተን፡ በመልኩ እንደፈጠራችሁ አውቃችኋል፤ አምናችሁማል፤ በዓለሙ ኹሉ፥ በተለይ፡ ሃይማኖታቸውን፡ በመጽሓፍ ቅዱስ ቃል ላይ በመሠረቱ ሕዝቦች ዘንድ፡ ተቀባይነትን አግኝቶ፡ ሲነገር እንደተኖረውና ተጽፎ እንደሚነበበው ማለት ነው።

ይህ እውቀት፡ ከእውቀቶች ኹሉ የላቀ፥ እምነቱም፡ ከእምነቶች ኹሉ በላይ ስለኾነ፡ "እንኳን፡ ለዚህ እውቀትና ለዚህ እምነት አበቃችሁ!" ያስሰኛል።

ታዲያ! በእግዚአብሔር መልክ መፈጠራችሁን፡ በእርግጥ ካወቃችሁና በእውነት ካመናችሁ፡ ይህ እውቀታችሁና ይህ እምነታችሁ፡ አረጋግጦ የሚያስገነዝባችሁ፡ 'ምንን ይኾናል!' ብላችሁ ታስባላችሁ?

አዎን! መልሳችሁ፡ "<u>እግዚአብሔርን መምሰል ነው።"</u> የሚል እንደሚኾን አይጠረጠርም።

መልካም! መልሳችሁ ይህ ከኾነ፡ እንግዲያ፡ "እግዚአብሔርን መምሰል!" ምንድን እንደኾነ፡ እስኪ ተናገሩ!

ለመኾኑ፡ እናንተ፡ የምትወልዱት፡ ወንድ ልጅና የምትወልዷት ሴት ልጅ፡ እናንተን መስለው፥ በእናንተ መልክ በመገኘታቸው አይደለም ወይ፡ እንደእናንተው፡ በወንድነትና በሴትነት ጾታ፡ "ሰዎች" ተብለው፡ እኩል፡ የሰውነት መብትና ሥልጣን፥ ክብርና ማዕርግ እንዲኖራቸው የሚደረገው? አዎን! በእርግጥ ነው።

ይህ እውነታ፡ እርግጠኛነቱ፡ እንዲህ የሚያስተማምን ከኾነ፡ እንደዚሁ ኹሉ፡ እግዚአብሔርን መስላችሁ፡ በእርሱ መልክ የተፈጠራችሁበት፡ ይህ ሰውነታችሁ፡ እርሱን ኾናችሁ ለመገኘት የመብቃታችሁ ማረጋገጫና ማሳመኛ ለመኾኑ፡ ምንም ጥርጣሬ ሊኖር፡ ከቶ አይችልም። እግዚአብሔር፡ እንዲህ አድርጎ፡ ራሱን አስመስሎና የእርሱ የኾነውን ኹሉ ሰጥቶ፡ በመልኩ ከፈጠራችሁ፡ ክፉውንና ደጉን ለይታችሁ አውቃችሁ፡ ክፉውን ትታችሁ፡ ደጉን በመያዝ፡ <u>እንደእርሱ፡ ቅኑን እንድታስቡ፥ እንደእርሱ፡ እውነቱን እንድትናገሩና እንደእርሱ፡ መልካሙን እንድታደርጉ ለመኾኑ፡</u> በምንም መልኩ ሊያጠያይቅና ሊያከራክር ከቶ አይችልም።

ታዲያ! እውነታው፡ ይህ ከኾነ፡ ለመኾኑ፡ ፍጡር ለኾነው ሰው፡ "እግዚአብሔርን ከመምሰል፡ የበለጠ ሀብትና ክብር ሊኖረው፡ ከቶ ይቻላልን? እግዚአብሔርስ፡ ለፍጡሩ ሰው፡ ከዚህ የሚበልጥ፡ ሊያደርግለት የሚያስፈልገው፥ ያላደረገለትም፡ የቀረ ነገር ይኖራልን?" ፈጽሞ የለም። "አለ!" ብሎ ማሰብ የሚቻለው ሰብአዊ፥ ወይም፡ መልአካዊ ፍጡር ሊገኝ አይቻልም።

እያንዳንዱ ሰብአዊ ፍጡር፡ በዚህ ዓለም፡ በሰብአዊነቱ፡ በትክክልና በእርግጥ የሚያውቀው፡ አንድ ነገር ብቻ አለ፤ ያም የሚያውቀው አንድ ነገር፡ ራሱን ነው።

እንዲህ፡ ራሱን፡ ፍጽሞ ያወቀ ከኾነ፥ ያ ራሱ ደግሞ፡ እግዚአብሔርን መስሎ፡ በእግዚአብሔር መልክ የተፈጠረ መኾኑን ያወቀና በዚህ እውቀት፡ ያመነበት ከኾነ፥ እግዚአብሔርንም፡ በእግዚአብሔርነቱ፡ ማለትም፡ በፈጣሪነቱና በአምላክነቱ፡ "አውቄዋለሁ!" ካለ፡ እንግዲያ፡ "እርሱ፡ ራሱ፡ እግዚአብሔርን፥ እግዚአብሔርም፡ እርሱን ኾነ!" ማለት አይደለምን? አዎን! ነው።

እናንተ ሰዎች! ወንዶችና ሴቶች ሆይ! እግዚአብሔር ያደረገው እውነታው እኮ፡ ይህ ነው! እስካኹን፡ አላወቃችሁምን? አልገባችሁምንስ? አልተረዳችሁትምን? እግዚአብሔር፡ በእየራሳችሁ ተፈጥሮ፥ በሥነ ፍጥረትና በመልእክተኞቹ አዋቂዎች፥ ነቢያትና ሐዋርያት አማካይነት እንድታውቁ፥ እንዲገባችሁ፥ እንድትገነዘቡና እንድታምኑ ሊያደርግ፡ በዚህ አግጣጫ፡ ለዝንተ ዓለም ሲያካኺደው የኖረው ጥረት፡ ይህ አልነበረምን?

ይህም አልሳካ ቢለው፡ ራሱ፡ ሰው ኾኖ፡ ወደዚህ ዓለም አልመጣምን? መጥቶስ፡ ስለዚሁ እውነታ፡ ለሰዎች፡ እየገለጸና እያብራራ ሲነገራቸው አልቆየምን? አዎን! ይህ ኹሉ ደርሷል፤ ኾኗል፤ተፈጽሟል።

እነዚህን እውነታዎች ከሚያረጋግጡ ቃላት መካከል፡ እስኪ፡ ጥቂቶቹን እየጠቃቀስን እናስታውሳችሁ!

፩. ሰው የኾነውና ራሱን፡ "የሰው ልጅ" እያለ ይጠራ የነበረው፡ እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ቃሉን ከሚያዳምጡት ተከታዮቹ መካከል፡ አንዱ፡ በንግግሩ መልእክት ተመሥጦ፡ "እባክህ፡ **እግዚአብሔር አብን አሳየንና ይበቃናል!**" ባለው ጊዜ፡ ምን ብሎ እንደመለሰለት ታውቁታላችሁ አይደለምን?

መልሱ፡ "**አንተ ፊልጶስ! ይህን ያህል ዘመን፡ ከእናንተ ጋር ስኖር፡ አታውቀኝምን?**" የሚል ነበር።

የእግዚአብሔር፡ አሳቡና ሥራው፥ ከሰው ይልቅ፡ የቱን ያህል የራቀና የተለየ እንደኾነ አያችሁ!? እስኪ፡ እንደገና፡ አስተውላችሁ ተመለከቱት!

"**አታውቀኝምን?**" ብሎ ሲጠይቀው፡ ምን ማለቱ ይመስለናል? "'እኔን አስመስዬ፡ በመልኬ ፈጠርሁህ!' ያልሁህ ፍጡሬ፡ በዚህ ተፈጥሮህ፡ 'አውቀኸኛል፤ በዚህ እውቀትህም አምነህ፡ ተቀብለኸኛል!' ብዬ ብመጣ፡ እንደማያውቅ እንግዳ ኾነህ፡ 'እግዚአብሔርን አሳየንና ይበቃናል!' ትለኛለህን? ምነዋ፡ ፊልጶስ!? እያየኸኝ!? ምነው፡ እንዲህ ብለህ ትጠይቀኛለህ? እኔ እኮ፡ አንተ ነህ! አንተ እኮ፡ እኔ ነኝ፤ እወቀኝ እንጂ። ይህ የምታየኝ፥ ይህ የማነጋግርህ፡ ማን መሰልሁህ? ዕሩቅ ብእሲ (ተራ ሰው)? ወይም፡ የማታውቀኝ፡ ልዩ ፍጡር ኾንሁብህን? የለም፣ አይደለም፤ እንደዚያ አይደለኹም።

"**እኔ እኮ፡ እግዚአብሔር ነኝ!** እንዴትስ አንተ፡ እንዲህ፡ በእውን እያየኸኝ፥ እንዲህም፡ እያነጋገርኸኝ፥ እንዲህም፡ እየዳሰስኸኝ፡ አኹን እንደገና፡ '**እግዚአብሔርን አሳየን!**' ትለኛለህ!?"

"ይህ ብቻ መሰለህ እንዴ!? አንተን፡ እንደእኔ አድርጌ ፈጥሬ፡ ወደዚህ ዓለም ከላክሁህ በኋላ፡ እኔ ደግሞ፡ ራሴን፡ አንተን አድርጌ፡ ይኸው፡ ወደዚህ ዓለም መጣሁ እኮ! ታዲያ! ይህ ሥራ፡ ምን ይመስልሃል? <u>አንተ፡ እኔን መኾንህን፥ እኔስ፡ አንተን መኾኔን ላሳይህ አይደለምን? ነው እኮ!</u> እስካኹን፡ ይህን አላወቅህምን? አላመንህምንስ? ካላወቅህና ካላመንህ፡ እንግዴህ ወዲህ፡ ብታውቅና ብታምን ይሻልሃል፤ ይጠቅምሃልም፤ እኔ፡ በእግዚአብሔርነቴም፥ በሰውነቴም፡ ፍጹም ተዋሕዶ፡ የመገለጤ እውነት መደምደሚያ፡ ይህ ነውና። አለዚያ፡ ይህን ካላወቅህና ካላመንህ፡ በብዙ የተጎዳህ ኾነህ ትቀራለህ።" (ዮሓ. ፲፬፥ ፰-፲፪።)

፪. አይሁድ፡ ጌታችን፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በእውነትና በብርሃን ትምህርቱ ተበሣጭተውና ተቆጥተው፡ በድንጋይ ሊወግሩት በተነሡ ጊዜ፡ ይህን ሊያደርጉ፡ ለምን እንደፈለጉ ምክንያታቸውን ሲጠይቃቸው፡ "ራስህን አምላክ በማድረግህ ነው!" ብለው እንደመለሱለት የተነገረውን ታስታውሳላችሁ።

እርሱም፡ "‹'እኔ፡ አማልክት ናችሁ!' አልሁ፤› ተብሎ በሕጋችሁ የተጻፈ አይደለምን? መጽሐፉ ሊሻር አይቻልምና፤ እነዚያን፡ <u>የእግዚአብሔርን ቃል የመጣላቸውን፡ 'አማልክት!' ካላቸው፡</u> 'የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ!' ስላልሁ፡ እናንተ፡ አብ የቀደሰውን፥ ወደዓለምም የላከውን፡ 'ትሳደባለህ!' ትሉታላችሁን?" ብሎ የመለሰውንም ታውቃላችሁ። (ዮሓ. ፲፥ ፴፩-፴፰።)

በዚህ መለኮታዊ ቃል መሠረት፡ በወንድነትና በሴትነት ጾታ ተለይቶ፡ ለኹለት ከመከፈሉ በፊት፡ "አዳም" ተብሎ፡ የተፈጠረው ሰው፡ በመጀመሪያ፡ በዚያው፡ ቀድሞ በተፈጠረበት፡ በእግዚአብሔርነት መልኩ፥ ቀጥሎም፡ በወንድነትና በሴትነት ጾታ ተለይቶ፡ ከኹለት ከተከፈለ በኋላም፡ "ከእኛ፡ እንደአንዱ ኾነ!" በተሰኘው አዋቂነቱ፡ ለአምላክነት በቅቶ፡ "አምላክ ነህ!" ለሚል፡ የእግዚአብሔር ማዕርግ ሊበቃ እንደሚችል ተረጋግጧል። ይኸውም፡ ሓሰትን ትቶ፡ እውነትን ሲፈጽም፥ ክፉውን ትቶ፡ መልካሙን ሲከተል፥ ሞትን ትቶ፡ ሕይወትን ሲመርጥ፡ ማለትም፡ በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነቱ ጸንቶ ሲገኝ ማለት ነው። ይህን እውነታ፡ ሊያስተባብል የሚቻለው ማንም ከቶ አይኖርም።

፫. ፍጥረተ ዓለሙ፡ ለመጨረሻው የትንሣኤ ዘጉባኤ ፍርድ በሚቀርብበት ጊዜ፡ እያንዳንዱ ሰብአዊ ፍጡር፡ ከፈጣሪው ፊት ቀርቦ የሚጠየቀው፡ <u>የሃይማኖቱ ፍሬ የኾነውን ምግባር ብቻ እንጂ፡</u> ሃይማኖቱን፥ ወይም፡ የሃይማኖቱን ዓይነት አለመኾኑ፥ ያም፡ የሃይማኖት ምግባር የኾነው ፍሬ፡ ለእየራሳችሁ፥ ወይም፡ ለሌላ ሳይኾን፡ <u>"ለእኔ ያደረጋችሁት!'</u>፥ ወይም፡ <u>"ለእኔ ያላደረጋችሁት!"</u> ብሎ መኾኑ ተነግሩዋል፤ በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ተጽፎ፡ ዘወትር ሲነበብ እንደሚደመጠው።

ማለትም፡ በዚያን ጊዜ፡ ለእያንዳንዱ ሰብኣዊ ፍጡር የሚቀርበው ጥያቄ፡ "ሃይማኖትህ/ሃይማኖትሽ ምንድን ነው? ወይም፡ ምን ዓይነት ሃይማኖት አለህ? አለሽ?" ተብሎ ሳይኾን፡ "በሃይማኖትህ/በሃይማኖትሽ፡ ምን በጎ ሥራን ሠራህ? ሠራሽ? ወይም፡ ምን አገልግሎትን አበረከትህ? አበረከትሽ?" ተብሎ መኾኑን፡ አስረግጦ የሚያስረዳና የሚያስጠነቅቅ መኾኑ ነው።

ቸሩ ፈጣሪ፡ ለእውነተኞቹና ለታማኞቹ ሰብኣውያን ፍጡሮቹ፡ "መልካሙን ኹሉ ስላደረጋችሁልኝ፡ ለእናንተው ፈጥሬ ያዘጋጀሁላችሁን፥ እናንተም፡ ወድዳችሁ የመረጣችኋትንና የቆያችሁባትን የእውነት መንግሥቴን፡ ለዘለዓለም ወርሳችሁ ትኖሩባት ዘንድ፡ ግቡባት!" ብሎ በሚቀበላቸው ጊዜ፡ **"መቼ አይተንህ ነው፡ ይህን መልካሙን ኹሉ ያደረግንልህ?"** ብለው ይመልሱለታል።

እግዚአብሔርም፡ **"አማን እብለክሙ! ኵሎ ዘገበርክሙ፡ ለአሓዱ፡ እምእሉ ንኡሳን አኀውየ፡ እለ የአምኑ ብየ፡ ሊተ ገበርክሙ።"** ማለትም፡ **"እውነት እላችኋለሁ፡ ከኹሉ ከሚያንሱ፡ ከእነዚህ፡ ለአንዱ፥ ወይም፡ ለአንዲቱ ያደረጋችሁት ኹሉ፡ ለእኔ አደረጋችሁልኝ!"** ይላቸዋል።

እንዲሁም፡ ለሓሰተኞቹና ለከሓዲዎቹ ፍጡሮቹ፡ "መልካም የኾነውን፡ አንዱንም እንኳ፡ ልታደርጉ ስላልፈለጋችሁ፡ ከእናንተ በፊት ተፈጥረው ለጠፉት፡ ለክፉዎቹ ሰይጣንና ለሠራዊቱ ወደተዘጋጀላቸው፥ እናንተም፡ ፈልጋችሁ ወደመረጣችሁትና ወደቆያችሁበት ወደዘለዓለም እሳት ኺዱ!" ብሎ በሚያሰናብታቸው ጊዜ፡ **"መቼ አይተንህ ነው፡ ይህን መልካሙን ኹሉ ያላደረግንልህ?"** ብለው ይመልሱለታል።

እግዚአብሔርም፡ **"አማን እብለክሙ! ዘኢገበርክሙ፡ ለአሓዱ፡ እምእሉ ንኡሳን አኀውየ፡ ሊተ ኢገበርክሙ።"** ማለትም፡ **"እውነት እላችኋለሁ፡ ከኹሉ ከሚያንሱ፡ ከእነዚህ፡ ለአንዱ፥ ወይም፡ ለአንዲቱ ስላላደረጋችሁት፡ ለእኔ አላደረጋችሁልኝም!"** ይላቸዋል። (ማቴ. ምዕራፍ ፳፭።)

አያችሁ! ከዚህ የተነሣ፡ ታላቁ እግዚአብሔር፡ እኛ፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ "የእኔ ብጤ!" የምንለውንና የምንላትን፡ እያንዳንዱንና እያንዳንዷን ምስኪን ደኃ፡ እንዴት <u>ራሱን</u> እያደረገ፡ ደጎችም ኾኑ ክፉዎች፡ በመጨረሻው ፍርድ፡ የዘለዓለም ዋጋን፥ ወይም የዘለዓለም ቅጣትን የሚቀበሉበትን መፋረጃ እንዳዘጋጀ? ይኸውም፡ እግዚአብሔር፡ እስከመጨረሻው ዝቅተኛ ደረጃ ድረስ ተዋርዶ፡ ራሱን፡ ከምን ያህሉ፡ የሰው ድህነት ጋር እንዳስተካከለ ማለት ነው።

እግዚአብሔር፡ ያንን/ያችን አነስተኛ ደኃ፡ "እኔ ነኝ!" ካለ፥ ያ/ያች አነስተኛ ደኃም፡ እግዚአብሔር ኾነ/ኾነች ማለት አይደለምን? አዎን! ኾነ። ኾነች።

እንግዴህ፡ በእነዚህ፡ ከላይ፡ በተጠቀሱት፡ በእግዚአብሔር ቃላት ምክንያት፡ የምንገነዘበው እውነት፡ እግዚአብሔር፡ ጥንቱኑ፡ ከመጀመሪያው እስከመጨረሻው፡ በሰውና በሰው፥ በሰውና በእግዚአብሔር መካከል እንዲኖር የፈለገውና የፈቀደው፥ የመሠረተውና የወጠነው፥ የተለመውና ያካኼደው የግንኙነት ሥርዓት፡ በሰውነትና በሰውነት፥ ወይም፡ በእግዚአብሔርነትና በሰውነት አቋም ሳይኾን፡ በኹለቱም ወገን፡ በእግዚአብሔርነቱ አቋማቸው ብቻ እንዲያበቃ መወሰኑን ነው። ይህም ማለት፡ ሰዎች፡ አንዳችን፡ ከአንዳችን፡ ማለትም፡ እርስ በርሳችን፥ ከዚያም አልፎ፡ ከእግዚአብሔር ጋር የሚኖረን ግንኙነት፡ በሰውነት ሳይኾን፡ በእግዚአብሔርነት መልክና ደረጃ እንዲኾን ፈቅዷል ማለት ነው።

እንዲህ ከኾነ፡ በሰዎች መካከል፥ በዓለምም ላይ፡ እንግዴህ፡ ምን ችግር ይኖራል? አንዳችም ችግር አይኖርም። እግዚአብሔር፡ የፈጠረውን፡ ሰብአዊ ፍጡሩን፡ እንዲህ፡ እንደራሱ፡ እንደእግዚአብሔር አድርጎ እያየው፡ መልካሙን እንዳደረገለትና እንደሚያደርግለት ኹሉ፡ በዚሁ ዓይነት፡ ሰው ኹሉ፡ ወንዱም ሴቱም፡ ሌላውን ወንድ፥ ወይም፡ ሌላዪቱን ሴት፡ እንዲህ እንደእግዚአብሔር እያየ፡ ቅኑን የሚያስብለት፥ ወይም፡ የሚያስብላት፥ እውነቱን የሚናገርለት፥ ወይም፡ የሚናገርላትና በጎውን የሚያደርግለት፥ ወይም፡ የሚያደርግላት ከኾነ፡ በዚያ ሰውነት ውስጥና በመሰሎቹ ወንዶችና ሴቶች መካከል፡ እንዴት ያለው ሰላምና ፍቅር፥ ብልጽግናና ደስታ ሊሰፍን ነው? አዎን! እውነተኛው ሰላምና ፍቅር፥ ብልጽግናና ደስታ በእርግጥ ይሰፍናሉ።

ከዚህ፡ ሦስተኛውና የመጨረሻው የብቅዓት ደረጃ ከኾነው፡ ከመንፈሳዊው ጸጋ ለመድረስ፡ በቅዱሱ ኪዳን፡ የኢትዮጵያ ተዋሕዶ ሃይማኖትና ምግባር፡ በየግል መጽናት፡ ለአንተ፥ ወይም፡ ለአንቺ፡ እጅግ አስፈላጊ ይኾናል። ይህን ጸጋ፡ እያንዳንዳችሁ፡ በእየራሳችሁ ፍላጎትና ገድል፡ ለእየራሳችሁ፡ በግል፥ ኹለታችሁም፡ በጋራ፡ የምታገኙት ነው። የጸጋው ተሳታፊዎች በምትኾኑበት፡ በዚያን ጊዜ፡ ለእናንተ፡ ሰው ኹሉ፡ እግዚአብሔር ይኾንላችኋል። እያንዳንዱን ሰው፡ የምታዩትና የምትቀበሉት፡ እንደቀደመው፡ የቅዱሱ ኪዳን ብሉያት ቃላት፡ "እግዚአብሔር ነው!" ብላችሁ ነው፤ እንደመጨረሻው የቅዱሱ ኪዳን ሓዲሳት ቃላት ደግሞ፡ ወንዱን፡ "ኢየሱስ ክርስቶስ ነው!" ሴቲቱንም፡ "ድንግል ማርያም ናት!" ብላችሁ ነው።

ታዲያ! እናንተ፡ በአንድ ወገን፡ ከእየራሳችሁ ጀምሮ፡ እየራሳችሁን፡ ለእግዚአብሔር መልክነት ከማብቃት ጋር፡ ሰውን ኹሉ፡ በዚሁ የእግዚአብሔርነት ደረጃ፥ ይኸውም፡ ወንዱን፡ እንደኢየሱስ ክርስቶስ፥ ሴቲቱንም፡ እንደድንግል ማርያም በማየት፡ ፍጹሙን የአክብሮትና የፍቅር በረከት ሰጥታችሁ፡ በዚያው የአክብሮትና የፍቅር መልክና ይዘት ተቀብላችሁ በምታገለግሉበትና በምታስተናግዱበት ጊዜ፡ በዚያኛው፡ በተገልጋዩ ወገን፡ የሚሰጣችሁ አስተያየትና የሚደረግላችሁ አቀባበል፡ ምን ዓይነት ይኾን? ይህን ጥያቄ፡ እናንተም፡ በየኅሊናችሁ ትጠይቁ ይኾናል።

አቀባበሉና ምላሹ፡ በአብዛኛው፡ ከእናንተ ምግባር ጋር ተመሳሳይ የኾነው ቅኑ፥ እውነቱና በጎው እንደማይኾን፡ አስቀድማችሁ፡ ማወቅና መጠበቅ ይኖርባችኋል። ያ ሳይኾን ቢቀር፡ ባማረ ነበር፤ ነገር ግን፡ አይደለም። እንዲያውም፡ በእውን ኾኖ የምታገኙት፡ ለእናንተ በጎ አሳብ፡ ተቃራኒና ተፃራሪ የኾነውን ክፉዉን አቋም ስለሚኾን፡ በዚህ ጊዜ፥ በዚህ ውጤት፡ በፍጹም ልትደነቁ አያስፈልግምም። ምክንያቱም፡ ከዚህ ዓለም ሰዎች፡ የሚጠበቀው ውጤት ይህ ስለኾነ ነው፤ በራሱ ስሕተትና ጉድለት የጠፋውን፡ ሰብአዊ ፍጡሩን ፈልጎ ሊያገኘው፥ አግኝቶም ሊያድነው፥ አድኖም፡ ወደተፈጠረበት ዘለዓለማዊነቱ ክብር ሊመልሰው በመጣው፡ ቸር ፈጣሪው ላይ፡ ሰብአዊ ፍጡሩ፡ የመለሰለት የባለውለተኛነት ዋጋ፡ በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ላይ በደረሰው፡ የመስቀል ፈተናና መከራ፡ እጅግ በዝቶ ታይቷልና።

ይኸው ፈጣሪያችሁ፡ ከእናንተ የሚጠብቀው፥ እናንተም፡ በየጎሊናችሁ፡ "ልናደርገው ይገባናል!" የምትሉት ድርሻ ቢኖር፡ ይህንኑ፡ በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነታችሁ፡ አስቀድማችሁ ጀምራችሁ፡ ከዚህ ያደረሳችሁትን፡ የእየራሳችሁን፡ የየግል ዕጣ ፋንታ፡ በእየፊናችሁ፡ አከናውናችሁ መገኘታችሁን ብቻ ነው።

## ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት በሚኖሩበት፡ የእግዚአብሔር ሥርዓት፡ ክህነትና መንግሥት፡ በተዋሕዶ፡ አንድ ናቸው።

ባለፉት፡ በኢትዮጵያ ትውልዶች መካከል፥ ዛሬም ባለው ትውልድ፥ ከዚህም አልፎ፡ በዓለም ሕዝቦች ዘንድ ሳይቀር፡ ከፍተኛና የጠለቀ ችግርን ፈጥሮ፡ ለዘመናት፡ እርስ በርስ ሲያስተላልቅ የኖረ፡ አንድ፡ ሥር የሰደደ፡ ክፉ ጠንቅ አለ።

ይኹን እንጂ፡ ይህ ጠንቅ፡ በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ዘንድ፡ ከጥንት ከመሠረቱም፡ ጨርሶ፡ ደብዛውም የለም።

ይህን ጠንቅ፡ ወደኢትዮጵያና ወደኢትዮጵያውያን አምጥተው፡ በቅዱሱ ኪዳን አገርና ሕዝብ ላይ፡ ለአያሌ ሽህ ዓመታት፡ በሥውር ማዳረስ ብቻ ሳይኾን፡ እስከዛሬም እንዲቀጥል ያደረጉት፡ ቀደም ብለው፡ ጣዖታውያኑ አረማውያን፥ ቀጥለውም፡ ኦሪታውያኑ አይሁድ፥ ከዚያም፡ ኦርቶዶክሳውያኑ ግብፆች መኾናቸው፡ ከዚህ በላይና ከዚህ በፊት፡ በየምክንያቱ፡ በሚበቃ ተብራርቶ ተገልጿል።

ይህ ቀሣፊ ጠንቅ የተከሠተው፡ በአዳምና ሔዋን የጋብቻ ቃል ኪዳን ተመሥርቶና በኖኅ የቀስተ ደመና ቃል ኪዳን ተገድግዶ፡ መልከ ጼዴቅ፡ በቍርባኑ አጽንቶ በቀጠለው፡ በቅዱሱ የእግዚአብሔር የቃል ኪዳን ሥርዓት፡ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ በመልካም እየሠሩበት ሣሉ፡ እኒያ፡ የኦሪቱ እስራኤላውያንና የኦርቶዶክሱ ግብፃውያን፡ ይህን፡ እግዚአብሔራዊዉን ኢትዮጵያዊ የቃል ኪዳን እውቀትና ሥርዓት፡ በእየራሳቸው የሰው ትምህርትና ወግ ለውጠው በመተካታቸው መኾኑ፡ በብርቱ ሊታወቅ ያስፈልጋል።

የእግዚአብሔር የኾነው፡ ኢትዮጵያዊው የቃል ኪዳን እውቀትና ሥርዓት፡ ስለእግዚአብሔር መንግሥት፡ የገለጸው እውቀትና የሰጠው ሥርዓት፡ ጠንቀኛ ከኾነው፡ ከእነዚያኞቹ፡ ከሰውኛው ትምህርትና ወግ፡ ፈጽሞ የተለየ ነው። የእግዚአብሔሩ፡ በአንድነትና በውሕደት፥ በኅብረትና በስምምነት የሚሠራ፥ ለመልካሙ የሕይወት ግብ የሚያበቃም ሲኾን፡ ሰውኛው ግን፡ በተናጠልና በልዩነት፥ በክፍፍልና በመቃረን የሚሠራና ለክፉው የሞት ግብ የሚዳርግ ኾኖ ተገኝቷል። ከዚህ ውጤቱ የተነሣ፡ ይህ ሰውኛው፡ ሰይጣናዊ መኾኑ፡ በግልጽ ተረጋግጦ ታውቋል፤ ከጥንት ጀምሮ፡ የእግዚአብሔርን መንግሥት እውቀትና ሥርዓት ሲያፈርስ የኖረው፡ እርሱ፡ "ሰይጣን፥ እባብ፥ ዘንዶ" የተባለው፡ ዲያብሎስ ነውና።

ታዲያ! ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ በቅዱሱ ኪዳን ጠብቀውት፡ ሲሠሩበት የኖሩት፡ ሥርዓተ መንግሥትና እውቀት፡ ከቶ ምንድን ነው? እርሱማ፡ <u>በአንድ ጊዜ፡ የእግዚአብሔር ልጅም፥ ካህንም፥ ንጉሥም በኾነው፡ በመልከ ጼዴቅ ቃል ኪዳን ምክንያት፡ እያንዳንዱ ሰው፥ በነፍስ ወከፍ፡ ወንድ ኾነ ሴት፡ ከአባቱ አብራክ ወጥቶ፡ በእናቱ ማሕፀን በሚፈጠርበት ጊዜ፡ ከእግዚአብሔር፡ በሥነ ፍጥረት በተሰጠው/በተሰጣት ባሕርያዊ ጸጋ፡ በአንድ ጊዜ፡ የእግዚአብሔር ልጅም፥ ካህንም፥ ነጋሢም የሚኾንበት/የምትኾንበት ሥርዓተ መንግሥትና እውቀት ነው።</u>

አስተውሉ! እነዚህ፡ ሦስት ጸጋዎች፡ ለወንዱ ብቻ ሳይኾን፡ ለሴቷም፡ በተፈጥሮ ጸጋነት የተሰጡ መኾናቸውን፥ "ኢትዮጵያዊ!" ወይም፡ "ኢትዮጵያዊት!" የሚያስሰኘውም፡ የዚሁ ጸጋ ባለቤትነት መኾኑን ተመልከቱት!

ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ ለዝንተ ዓለም ጠብቀውት የኖሩትን፡ ይህን እውቀትና ሥርዓት ነው፡ የአይሁድ ኦሪታውያንና የግብፅ ኦርቶዶክሳውያን፡ ለማፈራረስ ሞክረው፡ የእየራሳቸውን ሰብአዊ ትምህርትንና ወግን ለመተካት የደፈሩት። ይኸውም፡ "ቤተ ክህነትና ቤተ መንግሥት (Church and State) የተለያዩ ናቸው!" ደግሞም፡ "ሃይማኖት የግል፣ አገር የጋራ ነው!" በሚለው፡ ባዕድ ፈሊጣቸውና ስሑት ይትበሃላቸው ረቂቅ መሣሪያነት፡ ሲያካኺዱ የኖሩት አፍራሽ ተልእኮ ነው።

ይህ ባዕድ ፈሊጣቸው፥ ይህ ስሑት ይትበሃላቸው ነው እንግዴህ፡ ላለፉት ዘመናትና ለዛሬው የኢትዮጵያ ትውልድ ጭምር፡ ኃይለኛ ጠንቅ ኾኖ፡ የግልና የቤተሰብ፥ የብሔረሰብና የኅብረተሰብ፥ የአገረሰብና በጠቅላላ፡ የሰው ዘር አኗኗር፡ እንዲህ ምስቅልቅሉ እንዲወጣ፥ ፍጥረትም፡ እንዲህ እርስ በርሱ እንዲናጭና እንዲጨራረስ ያደረገው፤ እያደረገም ያለው።

ከዚህ የተነሣ፡ እስኪ! ከእየራሳችሁ ጀምሩና፡ እየራሳችሁን መርምሩ! እውነታውንም፡ ከእየራሳችሁ እያወጣችሁ ተመልከቱት! የኦሪታውያኑ አይሁድና የግብፃውያኑ ኦርቶዶክስ እምነትና ባህል፡ በኢትዮጵያ ትውልዶች ዘንድ፡ ሥር መስደድንና እየጸና መኼድን ከቀጠለበት፡ ከሦስት ሺሕና ከአንድ ሺሕ ስድስት መቶ ዓመታት ጀምሮ የኾነውንና እየኾነ ያለውን እዩት!

በእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ እና በእያንዳንዷ ኢትዮጵያዊት አእምሮ ላይ ተቀርፆ፥ በየልቦናቸውም ውስጥ አድሮ፥ ሰፍኖ የኖረው ልማድ፡ ከቶ ምን ዓይነት ነው? **"ቤተ ክህነት እና ቤተ መንግሥት የተለያዩ ናቸው!"** በሚለው፡ ከላይ በተጠቀሰው፡ ሰው ሠራሽ እውቀት ላይ የተመሠረተውና ከዚያ እየመነጨ ተስፋፍቶ የተንሰራፋው ዘይቤ [አባባል] አይደለምን? አዎን! በእርግጥ፡ እርሱ ነው። ይህንም እውነታ፡ ከዚህ የሚከተለው መግለጫ አጥርቶ ያሳያችኋል።

በቅድሚያ ግን፡ <u>እያንዳንዱ እውነተኛ ኢትዮጵያዊ፡ ሊኾንና ሊያደርግ፥ ሊልም የሚገባው፥ እያንዳንዷም እውነተኛ ኢትዮጵያዊት፡ ልትኾንና ልታደርግ፥ ልትልም የሚገባት፡ ምን እንደኾነ እናመልክታችሁ፤ ይህም፡ እንዲህ በሚለው፡ ሃይማኖታዊ ቃል ተገልጾ ይነበባል፦</u>

**"እኔ፡ በቅዱሱ ኪዳን ምክንያት፡ በተዋሕዶ፡ አንዲት በኾነችው፡ በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ፡ እንደመልከ ጼዴቅ፡ የእግዚአብሔር ልጅ፥ ካህንና ነጋሢ ነኝ፤ ባለኹበትም ኾኜ፡ እንደሙያዬና እንደፍላጎቴ፡ በቤተ ሕዝቡ፥ በቤተ ክህነቱና በቤተ ምልክናው የተግባር ዘርፎች ውስጥ፡ ራሴን በአግባቡ መድቤ፡ ነፍሳዊዉን፥ ሥጋዊዉንና መንፈሳዊዉን አገልግሎት የማበረክት ነኝ!"**

ይህን በማለት ፈንታ፦

በመጀመሪያ፡ እንዲህ፡ በተዋሕዶ ምሥጢር፡ አንድ የኾነውንና በነፍስ፥ በሥጋና በመንፈስ የተሠራውን እየራሳቸውን፡ በአንድ ወገን፡ "ሥጋዊ" እና "ጨዋ [ምእመን]"፥ በሌላው ወገን ደግሞ፡ "መንፈሳዊ" እና "ካህን [መነኵሴ]" ብለው፡ ከኹለት ለያይተው፥

ኹለተኛም፡ አኹንም፡ በተዋሕዶ ምሥጢር፡ አንዲት የኾነችውን፡ የእግዚአብሔርን መንግሥት፡ "ቤተ ክህነት" እና "ቤተ መንግሥት" በማለት፡ ከኹለት ከፋፍለው፡ እንዴት እስከዛሬ፥ ዛሬም፡ እርስ በርሳቸው እንደሚቀዋወሙና እንደሚቃረኑ፥ ከዚህም የተነሣ፡ በእየራሳቸው ላይ ብቻ ሳይኾን፡ በወገናቸውና በአገራቸው ላይ፡ ታላቁን ጉዳትና ጥፋት እንዳስከተሉ እዩት! ይኸውም፡ እንዲህ ነው፦

በቅድሚያ፡ ኹለቱም ወገኖች፡ ማለትም፡ ምሁሩ ካህንም ኾነ፥ ጨዋው ምእመን፡ በየፊናቸው ተስማምተው ከተቀበሉት፡ ከዚሁ፡ የእምነት አቋማቸው የተነሣ፡ የሚጋሩት መሠረታዊ አስተሳሰብ አለ፤ ይኸውም፡ "አዎን! ቤተ ክህነቱ እና ቤተ መንግሥቱ፡ እየራሳቸውን ችለው የተለያዩ ናቸው፤ ይኹን እንጂ፡ እንዲህም ኾነው፡ ጨርሰው የተለያዩ አይደሉም፤ የእየራሳቸውንና የጋራቸውን ጥቅም ለመጠበቅና ለማስጠበቅ ሲሉ፡ መረዳዳትና መተባበር አለባቸው!" የሚለው ነው። ይህ እንዳለ ኾኖ፡ በእያንዳንዳቸው በኩል ያለውን የተለያየ መሠረታዊ አስተሳሰብ ደግሞ፡ በአንክሮና በተዘክሮ፥ በትኵረትም፡ መመልከት አስፈላጊ ይኾናል።

በቅድሚያ፡ የጨዋው፥ ወይም፡ የምእመኑ አቋም ይገመገማል፡-

በአንደኛው ወገን፡ ከአጼው፥ ወይም፡ ከንግሥቲቱ አንሥቶ፡ በተዋረድ፡ እስከጭቃ ሹሙና እስከተራው ጨዋ ድረስ ያለው፡ ወንዱ ምእመንና መኰንን፥ ወይም፡ ሴቷ ምእመኒትና ወይዘሮ፡ ኹለቱም፡ ለእየራሳቸውና ለካህኑ የሚሉት ምን እንደኾነ፡ ባጭር አገላለጽ ቀርቧልና፡ እስኪ ስሙት!

"ቤተ መንግሥቱና ሥልጣኑ፡ የእኔ ነው፤ ወይም፡ እኔ፡ የቤተ መንግሥት ወገን ስለኾንሁ፡ መንግሥታዊው ሙሉ ሥልጣን፥ የፈላጭ ቆራጭነቱ ኃይልና ሥጋዊው ወታደርነት የእኔ የብቻዬ ነው!

"በቤተ መንግሥቱ በኩል ስላለው ሥልጣንና ሥራ፡ አንተን፡ ካህኑን አያገባህም። አንተ፡ በክህነትህ፡ ለእኔ፡ የሚገባኝን፥ እኔ የምመርጠውንና የምፈልገውን የክህነት አገልግሎት ብቻ፡ ያውም፡ ያንኑም ቢኾን፡ እኔ ስጠይቅህ፡ የምታበረክትልኝ ነው፤

"በአንተ በኩል፡ ለሥጋዊ ጥቅምህ የሚያስፈልግህን ከመጠየቅና ለእኔ ከመጸለይ በቀር፡ ስለነፍሴ፥ በሥጋዊውና በመንፈሳዊውም የግል ሕይወቴ ረገድ፡ አምልኮቴን፥ ጋብቻዬንና ትዳሬን፥ የባልና ሚስት አኗኗሬንና የልጆችን አስተዳደግ፥ ኅብረተሰባዊ ኑሮዬን ሳይቀር ስለሚመለከተው የሃይማኖትና የምግባር ሥርዓት፥ ይኼን፥ ይኼን አድርግ! አድርጊ! ወይም፡ አታድርግ! አታድርጊ!' ብለህ አትናገረኝ! አታስተምረኝ! አትምከረኝ! አታስገድደኝ!

"በተለይም፡ 'ንስሓ ገብታችሁ፡ ቍረቡ!' የሚለውን ቃል፡ ጨርሶ አታስሰማኝ! ሲቆርቡ ያደጉ፡ ሕፃናት ልጆች ቢኖሩኝም እንኳ፡ ወንዶቹ፡ ገና የጾታ ስሜት ሲያድርባቸው፥ ሴቶቹም፡ ገና የወር አበባ ማየት እንኳ ሳይጀምሩ፡ ቍርባኑን፡ በግድ ማቆም እንዳለባቸው፡ አንተው ካህኑ አውቀህ እንዳሳወቅኸኝ ታስታውሳለህ፤

"ይህን በሚመለከት፡ አንተ ከምታውቀው የባዕድ አምልኮ ምሥጢረኛዬ ጋር፡ በጨለማና በደም የተማማልሁት ድብቅ መሓላ ስላለኝ፡ ይህ ግዳጅ፡ በጥንቃቄ ተጠብቆ መፈጸም እንዳለበት፡ አንተም፥ እኔም ተገንዝበነዋልና፡ በዚህ ግዳጅ አፈጻጸም በኩል፡ በብርቱ እንደምትተባበረኝ፥ በዚህም መልክ፡ ከእኔ በኩል የማዝዝህን ኹሉ፡ ያለውልውል እንደምትፈጽም አምናለሁ።

"ለዚህ አገልግሎትህ፡ በእኔ በኩል፡ የሚያስፈልግህና አንተም፡ በምትጠይቅበት ጊዜ፡ ሥጋዊውና ዓለማዊው ነገር ኹሉ ይቀርብልሃል፤ ይስሰጥሃል፤ ይደረግልሃል። በቃ! አንተም፡ በዚሁ ተፈጠም! እኔም፡ ተፈጥሜአለሁ!"

በኹለተኛው ወገን ደግሞ፡ ከእጨጌው አንሥቶ፡ በተዋረድ፡ ሥልጣነ ክህነት እስካለው፡ እስከተራው ካህንና ሥልጣነ ክህነቱ ቀርቶ፡ ቅዱስ ቍርባንን እንኳ እስከማይቀበለው፡ እስከደብተራው ድረስ ያለው የቤተ ክህነቱ አገልጋይ፡ ከእየራሱ አልፎ፡ ለወንዱ ምእመንና መኰንን፥ ለሴቲቱም ምእመኒትና ወይዘሮ የሚለውን ስሙት!

"ቤተ ክህነቱና ሥልጣኑ፡ የእኔ ነው፤ ወይም፡ እኔ፡ የቤተ ክህነት ወገን ስለኾንሁ፡ መንፈሳዊውና ክህነታዊው ሥልጣን፥ አገልግሎቱም፡ የእኔ የብቻዬ ነው! እናንተን ምእመናኑን፡ ወንዶቹንም፥ ሴቶቹንም፡ አያገባችሁም።

"የመንግሥተ ሰማያት መግቢያ ቍልፍ፡ በእኔ እጅ ስለኾነ፡ ያለእኔ ፈቃድና ትእዛዝ፡ ወደእግዚአብሔር መንግሥት መግባት አትችሉም። ለአንተም፥ ለአንቺም፡ ሥጋዊዉን ኃይልና መንግሥታዊዉን ሥልጣን፡ እኔ ካላጸደቅሁላችሁ፡ ሕዝብን መግዛት አትችሉምና፡ ለእኔ ፈቃድና ፍላጎት ተገዢዎች መኾናችሁን ማረጋገጥ፥ ለዚህም፡ በፊቴ ጎንበስ እያላችሁ፡ በእጄ የያዝሁትን፡ የክርስቶስን መስቀል መሳለም አለባችሁ። ከግብፃውያን ላመጣሁትም የምንኵስናና የጵጵስና ባዕድ ማዕርጌና ሥልጣኔ፡ ከእግሬ ሥር እየሰገዳችሁ፡ ፈላጭ ቆራጭነቴን ታረጋግጣላችሁ።

"ለእናንተ፡ በነፍሳችሁና በመንፈሳዊው ሕይወታችሁ ረገድ ስላለው ደኅንነታችሁ፡ ከምጸልይላችሁ በቀር፡ እናንተን፡ ጨዋዎቹን፡ በሃይማኖትና በምግባር፥ እንዲሁም፡ በቤተ ክህነቱ ሥርዓት አጠባበቅና አወሳሰን በኩል፡ የሚያገባችሁ፡ አንዳችም ነገር አይኖርም።

"እናንተ፡ በጨዋነታችሁና በምእመንነታችሁ፡ ለእኔ፡ የሚገባኝን፥ እኔም፡ ለሥጋዬ ጥበቃና አገልግሎት፡ ያስፈልገኛል የምለውን ስጠይቃችሁ፡ ገንዘቡንና ሌላውን ስጦታ አበርክቱልኝ እንጂ፡ 'በእናንተ በኩል፡ ማናቸውንም ዓይነት፡ አምልኮ ባዕድ፡ ተዉ! ንስሓ እየገባችሁ፡ የኢየሱስ ክርስቶስን፡ ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙን ተቀበሉ! አትፋቱ! ይልቁንስ፡ ጋብቻችሁን፡ በሥርዓተ ተክሊልና በቅዱስ ቍርባን ቀድሱ! ልጆቻችሁንም፡ በዚሁ መንገድ እያስተማራችሁና እየመከራችሁ፥ እየገሠፃችሁና እየመራችሁ፡ አሳድጉ!" እያልሁ፡ አልነግራችሁም፤ አላስተምራችሁም፤ አልመክራችሁም፤ ፈጽሜ አላስቸግራችሁም፤ አላስገድዳችሁም፤ አላስታውሳችሁምም።

"ይኹን እንጂ፡ ሴትንና በሴትነቷ እንድትኖረው፥ ከወላድነቷ ጋር በተያያዘም፡ በተፈጥሮ የተሰጣት ግዳጅ ኹሉ፥ በጠቅላላ፡ የእርሷን ሕይወት በሚመለከት የተደነገገው ኹሉ፡ እንደኦሪቱ ሕግጋት፡ ርኵሰትና መርገም ስለኾነ፡ ይህ ጽኑ ልማድ ተጠብቆ ስለመቀጠሉ፡ በእናንተም፥ በእኔም በኩል፡ ብርቱ ጥንቃቄ መደረጉ መቀጠል እንዳለበት እንዳትዘነጉት ያስፈልጋል። በቃ! እናንተም ተፈጠሙ! እኔም፡ ተፈጥሜአለሁ።"

ይኼ ዓይነቱ ጠንቀኛ የእምነት መሠረታዊ አስተሳሰብና አሠራር ነው እንግዴህ፡ ይህን፡ ከ፫ (ሦስት) ሺሁና ከ፩ሺ፮፻ (አንድ ሽሕ ስድስት መቶው) ዓመታት ጀምሮ፡ "ኢትዮጵያዊ ነኝ!" የሚለውን ትውልድ፥ የዛሬውን ጨምሮ፡ እርስ በእርሱ ሲያናቍርና ሲያስተላልቅ፥ ወደኋላም ሲያስቀር የኖረው፥ ለአኹኑ ውርደትና ውድቀትም ያደረሰው! ይህ ዓይነቱ አስተሳሰብና አሠራር፡ እውነተኛው የእግዚአብሔሩ ሳይኾን፡ ሰው-ሠራሹና ሰይጣናዊው መኾኑ፡ ለማንም አስተዋይ ተመልካች፡ በቀላሉ ተለይቶ ይታወቃል።

## በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ሥርዓት፡ ኢትዮጵያዊውና ኢትዮጵያዊቷ፡ እያንዳንዳቸው፡ ምእመን፥ ካህን እና ነጋሢ ናቸው።

ይህ እውነታ፡ በቀላሉ፡ ተለይቶ የሚታወቅበት፡ ግልጥ ማረጋገጫ አለ፤ ይኸውም፡ በእያንዳንዱ እውነተኛ ኢትዮጵያዊ እና በእያንዳንዷ እውነተኛ ኢትዮጵያዊት ልቦና ውስጥ ተጽፎና ተቀርጾ፥ በበለጠ ጸንቶና ታትሞም የኖረው፥ ዛሬም ያለው ነው፤ እርሱንም፡ እንዲህ በሚል፡ አጭር ቃል መግለጽ ይቻላል፦ "የእናት አገሬ ኢትዮጵያ፡ የመንግሥቷና የሕዝቧ፥ የቤተ ክህነቷ (የሃይማኖቷ) እና የቤተ ምልክናዋ (የአስተዳደርዋ) ጉዳይ አይመለከተኝም፤ አያሳስበኝም፤ አያስጠይቀኝም!" የሚል፡ አንድም ጨዋ፥ ወይም፡ አንድም ካህን፣ ወንድ፥ ወይም፡ ሴት፡ ሊገኝ/ልትገኝ የማይቻል መኾኑ ነው።

በሌላ አገላለጽ፡ የቤተ ሕዝቡ አባል የኾነው፡ ምእመን፥ ወይም፡ ጨዋ፡ ወንድ፥ ወይም፡ ሴት፡ ከልቡ፡ "በኢትዮጵያ ጉዳይ፡ እኔን የሚያሳስበኝ፡ ቤተ መንግሥቱን የሚመለከተው ብቻ ነው! ስለቤተ ክህነቱ ግን፡ እኔን አያሳስበኝም! አይመለከተኝም! አያስጠይቀኝምም!" ሊል የሚችል አለመኖሩ ነው፤ ምእመኑ፥ ጨዋው፡ ወንዱም፥ ሴቱም፡ በቤተ ሕዝብ አባልነቱ፡ የቤተ መንግሥቱም፥ የቤተ ክህነቱም ጉዳይ፡ እኩል ይመለከተዋልና፤ ያሳስበዋልምና፤ ያስጠይቀዋልምና።

እንደዚሁ ኹሉ፡ የቤተ ሕዝቡ አባል የኾነው፡ ካህኑም፡ "በኢትዮጵያ ጉዳይ፡ እኔን የሚያሳስበኝ፡ ቤተ ክህነቱን የሚመለከተው ብቻ ነው! ስለቤተ መንግሥቱ ግን፡ እኔን አያሳስበኝም! አይመለከተኝም! አያስጠይቀኝምም!" ሊል የሚችል አለመኖሩ ነው፤ ካህኑ፡ በቤተ ሕዝብ አባልነቱ፡ የቤተ ክህነቱም፥ የቤተ መንግሥቱም ጉዳይ፡ እኩል ይመለከተዋልና፤ ያሳስበዋልምና፤ ያስጠይቀዋልምና።

በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት በተገኘው፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ተዋሕዶ ሃይማኖት ጸጋ፡ ካህኑም፥ ምእመኑም፥ ወንዱም፥ ሴቱም፥ በየግል ሰውነታቸው፡ ኹሉም፡ እኩል፡ የቤተ ሕዝቡ፥ የቤተ ምልክናውና የቤተ ክህነቱ አባሎች ናቸው። ስለዚህ፡ በኹሉም ዓይነት አገልግሎት፥ ኀላፊነትና ግዳጅ፡ ኹሉንም፡ እኩል ይመለከታቸዋል፤ ያሳስባቸዋል፤ ያስጠይቃቸዋልም።

በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ፡ "ይህ፥ ይህ፡ የካህኑ ብቻ ነው! እርሱን ብቻ የሚመለከት ነው። ጨዋውን፥ ምእመኑን አይመለከተውም። ይህ፥ ይህ ደግሞ፡ የምእመኑ ብቻ ነው፤ ካህኑን፡ አይመለከተውም።" የሚባል ነገር ከቶ የለም። እያንዳንዱና እያንዳንዷ፡ እንደየችሎታቸውና እንደየሙያቸው፡ ቤተ ክህነቱንም፥ ቤተ መንግሥቱንም፥ ኹሉንም፥ እያንዳንዱንም መኾን ይችላሉ።

ሌላው ቀርቶ፡ በቤተ ሕዝቡ፡ ሕዝባዊ ፥ በቤተ ምልክናው፡ መለካዊ፥ በቤተ ክህነቱም፡ ክህነታዊ ለኾነው አባልነትና አገልግሎት እንኳ፡ "ይህ የወንድ ነው፤ ይህ፡ የሴት ነው!" እየተባለ፡ ምንም ዓይነት፡ ልዩነት ከቶ አይደረግም። ኹሉም፡ በየተጠራበት ያገለግላል እንጂ። ደግሞም፡ ወንዱ፡ "እኔ ወንድ ነኝ፤ በወንድነቴ፡ ይኼ ይኼ ሥልጣን፡ የእኔ፡ የብቻዬ ነው፤ አንቺ፡ ሴት ነሽ፤ መብትሽ፡ እስከዚህ ድረስ የተገደበ ነው!" ሴቷም፡ "እኔ ሴት ነኝ፤ በሴትነቴ፡ ይኼ ይኼ ሥልጣን፡ የእኔ፡ የብቻዬ ነው፤ አንተ፡ ወንድ ነህ፤ መብትህ፡ እስከዚህ ድረስ የተገደበ ነው!" የሚባባሉበት ኹኔታ ጨርሶ የለም።

ወንድ የኾነ ኹሉ፡ እየራሱን፡ እንደቀደመው አዳም ካላደረገ በቀር፥ እንዲሁም፡ ሴት የኾነች ኹላ፡ እየራሷን፡ እንደቀደመችዪቱ ሔዋን ካላደረገች በቀር፡ <u>በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ፡ ወንድ ኹሉ የሚታየው፡ ኢየሱስ ክርስቶስን መስሎ ነው፤ ሴት ኹላ የምትታየው፡ ድንግል ማርያምን መስላ ነው።</u> ይህ ሃይማኖታዊና ምግባራዊ እውነታ፡ በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ዘንድ፡ ከጥንት ጀምሮ፡ መደበኛ ሥርዓት ኾኖ ኖርዋል፤ ዛሬና ወደፊትም፡ ለዘለዓለም ይኖራል።

እንግዴህ፡ የዛሬው ትውልድ አባሎች የኾኑት፡ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ እያንዳንዳቸው፡ በነፍስ፡ ወከፍ፡ እየራሳቸውንና ኢትዮጵያዊ ማንነታቸውን፡ ይህን ከመሰለው፡ አኹን ከተደረሰበት ውርደትና ውድቀት፥ ከመጨረሻውም የጥፋትና የድምሳሴ ፍጻሜ፡ ለማዳን፡ መፍትሔው መንገድ፡ አንድ ብቻ ኾኖ ይገኛል፤ ሌላ ማማረጫ የለም።

እርሱም፡ እያንዳንዱ እውነተኛ ኢትዮጵያዊና እያንዳንዷ ኢትዮጵያዊት፡ ከላይ ቀደም ብሎ የተገለጠውን፡ "እኔ፡ በቅዱሱ ኪዳን ምክንያት፡ በተዋሕዶ፡ አንዲት በኾነችው፡ በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ፡ እንደመልከ ጼዴቅ፡ የእግዚአብሔር ልጅ፥ ካህንና ነጋሢ ነኝ፤ ባለኹበትም ኾኜ፡እንደሙያዬና እንደፍላጎቴ፡ በቤተ ሕዝቡ፥ በቤተ ክህነቱና በቤተ ምልክናው የተግባር ዘርፎች ውስጥ፡ ራሴን በአግባቡ መድቤ፡ ነፍሳዊዉን፥ ሥጋዊዉንና መንፈሳዊዉን አገልግሎት የማበረክት ነኝ!" የሚለውን ማረጋገጫ ቃል፡ በሃይማኖትም፥ በምግባርም፡ እውንና ሕይወት አድርጎ፡ መኖር ነው።

ከዚህ የተነሣ፡ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ እና እያንዳንዷ ኢትዮጵያዊት፡ ባያውቁት ነው እንጂ፡ ቢያውቁት፥ ወይም፡ በሚያውቁበት ጊዜ፡ እንግዴህ ወዲህ፡ እየራሳቸውን የሚያገኙትና ለእየራሳቸው የሚሉት ይህ ነው፡-

"እኔ፡ ምእመን ብቻ፥ ወይም፡ ካህንም ብቻ አይደለሁም፤ እንደመጀመሪያው መልከ ጼዴቅና እንደመጨረሻው መልከ ጼዴቅ፡ እንደኢየሱስ ክርስቶስ፡ <u>የእግዚአብሔር ምእመንም፥ ልጅም፥ ካህንም ነኝ!</u> ይህ ብቻ አይደለም፤ እንደመጀመሪያው መልከ ጼዴቅና እንደመጨረሻው መልከ ጼዴቅ፡ እንደኢየሱስ ክርስቶስ፡ <u>የእግዚአብሔር መንግሥት፡ ወራሽም፥ ነጋሢም ነኝ!</u>

"በንጽሓ ጠባይ በተሠራሁበት፡ ጥንተ ተፈጥሮዬ፡ እግዚአብሔርን መስዬና እንደእርሱ ኾኜ፡ በአምላክ መልክ የምኖርበት ሰብእና አለኝ፤ እርሱም፡ ከቅድስት ድንግል ማርያም በተገኘው፡ በመለኮት፡ የትስብእት ሥጋና ደም ቤዛነት፡ ከክፋት፥ ከኃጢአትና ከሞት ድኖ፡ በክርስቶስ ትንሣኤ ታድሷል፤ በዕርገቱም፡ ወደቀደመ ክብሩ ተመልሷል።

"ስለዚህ፡ እኔ፡ ዛሬ፡ በዚች ምድር ላይ ሰፍና፡ በካህኑ ንጉሥ ኢየሱስ ክርስቶስ አባትነት እና በካህኒቱ ንግሥት ድንግል ማርያም እናትነት፡ ፍጥረተ-ዓለሙን በምትመራውና በምታስተዳድረው፥ በምትጠብቀውና በምትመግበው፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ፡ በሥጋዬና በነፍሴ፥ በመንፈሴና በኹለንተናዬ፡ የእግዚአብሔር ልጅ፥ የእግዚአብሔር ካህንና የእግዚአብሔር ነጋሢ ኾኛለሁ።

"ከዚህ ጋር፡ ከመንፈስ ቅዱስ በታደልሁት እውቀቴና በተፈጥሮ ዝንባሌዬ ባገኘሁት ሙያዬ፡ ነፍሳዊዉን፥ ሥጋዊዉንና መንፈሳዊዉን አገልግሎቴን፡ ፈጣሪዬ በወሰነልኝ ቦታ ተገኝቼ፡ በቤተ ሕዝቡ፥ በቤተ ክህነቱና በቤተ ምልክናው የተግባር ዘርፎች ውስጥ፡ እንደቅድስት ድንግል ማርያምና እንደጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለማያቸው የተፈጥሮ ወገኖቼ እያበረከትሁና እያካኼድሁ፡ በፍቅርና በሰላም፥ በደስታና በምስጋና እኖራለሁ።

"ይህም፡ በመጀመሪያው የመንፈስ ትንሣኤና በዘለዓለማዊት ሰንበት የምኖረው ሕይወቴ ነው።"

እንዲህ ከኾነ፡ እንግዴህ ወዲህ፡ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ እና እያንዳንዷ ኢትዮጵያዊት፡ ምን የሚፈልጉት፥ ምንስ የሚያጡት ነገር ይኖራል? ኹሉ፡ የእነርሱ ኾነ አይደለምን? እስከንጉሥነትና ንግሥትነት የሚያደርሰው ሥልጣንና ኃይል፥ እስከኅዋ ሥነ-እውቀትና የጠፈር ኪነ ጥበብ ሊቅነት የሚያደርሰው፡ የምሁርነት ማዕርግና የፍልስፍና ክብር፥ እስከመላው ዓለም የሀብትና የገንዘብ ባለቤትነት የሚያደርሰው ብልጽግና ሳይቀር፡ ኹሉ፡ ለእነርሱ ኾነ አይደለምን? ከእነዚህ ጊዜያዊና ምድራዊ ይዞታዎች ግብ ለመድረስ፡ ሰላምንና ፍቅርን፥ ደስታንና ዕረፍትን አጥተው፥ በምኞት እየተቃጠሉ፡ ከእየራሳቸውና ከሰው፥ ከፈጣሪያቸውም ጋር ሲጣሉ ከመኖር ነጻ ወጡ አይደለምን? በየሙያ መስካቸው፡ የሚማሩትና የሚሠለጥኑበት፥ የሚያጠኑትና የሚመራመሩት ኹሉ፡ ለአገልግሎት ጥቅምና ለመልካም ተግባር ሊውል አይደለምን? አዎን! የሚኾነው እውነታ፡ በእርግጥ ይኼ ነው።

**ይህን ኹሉ፡ የእግዚአብሔርን እውነት፡ የምታውቁበት የእውቀት ብርሃን።**

ይህን እውነታ፡ ገሃድ አድርጎ የሚያሳውቃችሁ ተጨባጩ የኃይል ምንጭና የትርኢቱ መድረክ፡ በሦስቱ አካላትና ባሕርያት ተከናውኖና ተዋሕዶ፡ በፈጣሪ ኪነ ጥበብ የተሠራው፥ ዕፁብ ድንቅም የኾነው፡ ነፍሳዊው፥ ሥጋዊውና መንፈሳዊው የተፈጥሮ ሰውነታችሁ ነው።

ከመለኮት ተከፍላ፡ በዚህ የሥጋ አካልና ባሕርይ የገዘፈችው ነፍስ፡ በዚህ አካሏና ባሕርይዋ፡ ከመጨረሻው፡ የመንፈስ አካልና ባሕርይ ጋር ተዋሕዳ የምትኖር ናት።

ይህች ነፍስ፡ ሥጋዋን ጨምራ፡ ከክፉውና ከርኵሱ ይልቅ፡ መልካምና ቅዱስ የኾነውን መርጣ፡ በዚህ በተዋሓደችው፡ የእውነት መንፈስ ፈቃድ የምትመራ በምትኾንበት ጊዜ፡ ከሥጋዊው እውቀት በላይ የኾነው፡ ይህ ኹሉ፡ ጥልቁና ምጡቁ መንፈሳዊ እውቀት ይከሠትላታል። በእውቀቱ፡ ፈጽማ ትሞላለች፤ የማታውቀው ነገር፡ ከቶ አይኖርም።

ይህን እውቀት ስታገኝ፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ፡ የቅዱሱን ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ሕይወት፡ በፍጹም ነጻነትና ሰላም፥ ፍቅርና ደስታ መኖር ትጀምራለች፤ ለዘለዓለምም ትኖርበት ዘንድ፡ በዚሁ ህልውናዋ ትቀጥላለች።

ይህም ማለት፡ ነፍስ፡ አስተሳሰቧንና ሕይወቷን የምትመራው፡ በእውነተኛውና በመልካሙ መንፈስ ሳይኾን፡ ከዚያ ይልቅ፡ ወደሓሰተኛውና ወደክፉው በሚያዘነብለው፡ በሥጋዊው አእምሮዋና ኃይሏ፥ ፈቃዷና ፍላጎቷ ብቻ በመወሰን ከኾነ፡ ከላይ የተጠቀሰውን፡ የቅዱሱን ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ሕይወት ልታውቀው፥ ልታገኘውም፥ ልትኖረውም አይቻላትም።

ማንኛውም ሰው፡ ወንድ ኾነ ሴት፥ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ፡ የቅዱሱን ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ሕይወት አግኝቶ፡ በፍጹም ነጻነትና ሰላም፥ ፍቅርና ደስታ ለዘለዓለምም መኖር የሚችለው፡ ሰውኛው ትምህርት ሳያስፈልገው፡ ከእግዚአብሔር፡ በተፈጥሮ በተሰጠው እውቀቱ ብቻ በመጠቀም መኾኑ፡ "ኢትዮጵያዊ/ት ነኝ!" በሚለውም ኾነ፡ በሌላው ሰብአዊ ፍጡር ዘንድ ሊታውቅ ይገባል። ከሰውኛው ትምህርት ይልቅ፡ የሚሻለውና የሚበጀው፥ የሚበልጠውና የሚጠቅመውም፡ ከእግዚአብሔር፡ በተፈጥሮ የተሰጠው እውቀት ነውና።

## መደምደሚያ

በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ፡ መልካሙና ዘለዓለማዊ የኾነው፡ የሰብአዊው ፍጡር ሕይወት፥ ህልውናው [አኗኗሩ]፡ እንግዲህ፡ ይኼ ነው።

ስለዚህ፡ እያንዳንዳችሁ፡ እየራሳችሁን፡ ደካማና ሰነፍ፥ ለሌላው ለክፉው መንፈሳዊና ሥጋዊ ኃይል ተገዢ፥ ከዚያም አልፋችሁ፡ ባርያ አታድርጉ! እግዚአብሔር በመልኩ እስከመፍጠር ያደረሰውንና "ከእኛ እንደአንዳችን ኾናችኋል!" ያሰኛችውን ፍጹሙን እውቀቱን የለገሠበትን፡ ይህን የመሰለውን፡ የመጨረሻውን የክብርና የሥልጣን ደረጃ ያቀዳጃችሁ፡ ለምን እንደኾነ፡ በትክክል አውቃችሁ፡ ከልባችሁ ልትገነዘቡት ይገባችኋል።

በሥጋም፥ በነፍስም፥ በመንፈስም፥ በአጠቃላይ፡ በየኹለንተናችሁ፡ እየራሳችሁን ችላችሁ፥ በእርሱ፡ በፈጣሪያችሁና በቅድስት እናቱ ክብርና ሥልጣን፡ የእየራሳችሁ ጌታ/እመቤት ኾናችሁ፡ ክፉትና ኃጢአት ሥቃይና ሞት የሌለበትን፥ የእርሱ የኾነውን፡ መልካሙን፡ የትንሣኤና የሰንበት ሕይወት፡ ለእየራሳችሁና እርስ በርሳችሁ፡ በፍጹም ሰላምና ፍቅር፥ ደስታና ብልጽግና እንድትኖሩት ነው እንጂ፡ እንዲህ፡ እየራሳችሁን በደካማነትና በተገዢነት አዋርዳችሁ፥ የሰይጣንና የክፉ ሰዎች ባሪያዎች እንድትኾኑ፥ እርስ በርሳችሁም እየተጣላችሁ እንድትካሰሱና እንድትጋደሉ አይደለም።

ጥንቱኑም ቢኾን፡ እያንዳንዳችንን፡ በዚህ መልኩና ሥልጣኑ የፈጠረንና ወደዚህ ዓለም ያመጣን፡ በሥጋችንም፥ በነፍሳችንና በመንፈሳችንም፡ እንድንራብና እንድንጠማ፥ እንድንራቆትና እንድንታመም፥ እንድንታሠርና እንድንንከራተት፥ በጠቅላላ፡ እንድናጣና እንድንቸገር፥ ከዚህ የተነሣና በተለያዩ ምክንያቶችም፡ ክፉትን ፀንሰንና ኃጢአትን ሠርተን፡ በመጨረሻ፡ ተሠቃይተን እንድንሞት አይደለም።

አዎን! እግዚአብሔር በመልኩ፡ እርሱን አስመስሎ፥ በክብሩም፡ የእርሱ የኾነውን አቀዳጅቶ የፈጠረው የሰው ልጅ፡ ለራሱ የሚገለገልበትንና ፍጥረቱን የሚያገለግልበትን፡ ቤተ ሕዝቡን፥ ቤተ ምልክናውንና ቤተ ክህነቱን፡ እንደነፍስ፥ እንደሥጋና እንደመንፈስ፡ በተዋሕዶ፡ አንድ አድርጎ፡ ይመራበትና ይተዳድርበት ዘንድ፡ ቸሩ ፈጣሪው እግዚአብሔር፡ አሳምሮና አደላድሎ፥ አሟልቶና አጥርቶ የሰጠውን፡ ይህን ሥርዓተ መንግሥትና እውቀት ነው፡ ሰይጣናዊው ኃይል አፈራርሶ ሊተካ የሚሞክረው። ነገር ግን አይቻለውም፤ ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ በነጻነት ህልውናዋ፡ እስከዛሬ ኖራለች፤ ዛሬም አለች፤ ለወደፊቱም፡ ይኸው፡ እንደቀጠለች ትገኛለች።

የዚች፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ኢትዮጵያ፡ የመነሻና የመድረሻ ዓላማዋ፡ አንድና አንድ ብቻ ነው፤ እርሱም፡ እያንዳንዱ ሰብአዊ ፍጡር፡ ከእግዚአብሔር በተፈጥሮ በተሰጠው፡ በሥጋዊው፥ በነፍሳዊውና በመንፈሳዊው የመብትና የሥልጣን ጸጋ እየተጠቀመ፡ በውስጡ ያለውንና ዐብሮት የተፈጠረውን የእግዚአብሔርን እውቀት፡ ከራሱና በራሱ እየገለጠ፡ በሃይማኖት የብቅዓት ደረጃ ተገንዝቦት እንዲቀበለው፥ አውቆም፡ በምግባር የብቅዓት ደረጃ፡ በሥራ ላይ ዐውሎት፡ በሕይወትነት እንዲኖረው ማድረግ ነው።

እንዲህ ከኾነ፡ እያንዳንዳችሁ የተፈጠራችሁትና ወደዚህ ዓለም የመጣችሁት፡ በእየግላችሁ፡ ለእየራሳችሁ ነው፤ የምትኖሩትም፡ በቅድሚያ፡ በእየግላችሁ፡ ለእየራሳችሁ ነው፤ መለኮታዊው የዕረፍት ጥሪ ሲደርሳችሁ፡ የዚህ ዓለም እንግድነታችሁን ጨርሳችሁ የምትሰናበቱትም፡ በእየግላችሁ፡ በእየራሳችሁ ነው። በዚህ ረገድ፡ እየራሳችሁ፡ ለእየራሳችሁ ኀላፊዎች ናችሁ እንጂ፡ ለእናንተ የሚያልፍላችሁ፡ ሌላ፡ ማንም የለም፤ እናንተም፡ የምታልፉለት ከቶ የለም።

ስለዚህ፡ ውሳኔው፡ የየአንዳንዳችሁ ነው!!!

እንግዴህ፡ እንደቅዱሱ ኪዳን እምነታችን፡ በዓለም ላይ፡ በፈጣሪ በኩል፡ ለፍጥረቱ፡ ሳይደረግለት የቀረ፥ የሚጠበቅ፡ አንዳችም ነገር፡ ከቶ የለም።

የፍጥረቱ ሥሪና ባለቤት በኾነው፡ በእርሱ፡ በአንዱ አምላክ በእግዚአብሔር አብ፥ ሕይወቱ በኾነው፡ በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ፡ ዕፁብ ድንቅ ግብር፡ ከፍጽምት፡ ቅድስት ድንግል ማርያም፡ በፍጹም ሰውነት በተወለደው፡ በልጁ፡ በእግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ኹሉ ነገር፡ ለአንዴና ለዘለዓለሙ አብቅቷል፤ ተጨርሷል፤ አልቋል፤ ተደርጓል፤ ተፈጽሟል። ይህም፡ እግዚአብሔር አምላክ፡ በፍጥረቱ የከሠተው እውነትና የፈጸመው መልካምነት፥ ለፍጥረቱ የሰጠው ተስፋና ያናገረው ትንቢት፥ ያሳደረው ፍላጎትና ያሳየው ሕልም፥ የገለጠው ራእይና የተካየደው ቃል ኪዳን፥ የለገሠው ቸርነትና ያደረገው ምሕረት ነው።

ስለዚህ፡ በሌሎች ላይ ኾኖና እየኾነ ያየነውና የምናየው፡ የሰማነውና የምንሰማው፡ የሞቱ ጥሪ፥ ወይም፡ ደምሳሹ የጥፋት ኃይል፡ በእኛም ላይ ድንገት ደርሶብን፡ ያለንስሓ እንዳንወሰሰድ፡ አንተም፥ አንቺም፡ ኹላችሁም፡ ለአንዲት አፍታም እንኳ ቢኾን፡ ቀጠሮ ሳትሰጡ፡ እየራሳችሁን፡ ለእውነተኛው የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ሕይወት ዐብቅታችሁ ተገኙ! የእግዚአብሔር መንግሥት ኢትዮጵያ፡ ለግዙፉ ፍጥረተ ዓለም፡ የመገለጫዋ ቀን፡ እነሆ ደርሷልና! የዚህም፡ የምሥራች ዜና፡ በቅርቡ በሚወጣው፡ የአዋጅ ቃል ይነገራል።

ዘለዓለማዊው ሊቀ ካህናታችንና ንጉሠ ነገሥታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡"**አነ ውእቱ፡ አልፋ ወአ! አነ ቀዳማዊ፥ ወአነ ደኃራዊ! ርእስ፥ ወማኅለቅት! ወናሁ እመጽእ ፍጡነ፤ ወእሤትየኒ ምስሌየ ውእቱ፡ ከመ እፍድዮ ለለአሐዱ፤ ወእኰንኖ በከመ ምግባሩ። ወኢትሕትም ቃለ ተነብዮቱ፡ ለዝንቱ መጽሐፍ፡ እስመ በጽሐ ዘመኑ። ወለዘገፍዐኒ፡ ይገፍዕዎ እንከ! ወለዘረስሓኒ ያረስሕዎ እንከ! ወጻድቅ፡ ለይጽድቅ! ወንጹሕኒ፡ ለይንጻሕ!**"

ማለትም፡ "**እኔ፡ የኹሉ፡ መጀመሪያና መጨረሻ፥ ራስና መደምደሚያ ነኝ! ለቃልነቴ መገለጫ፡ መነሻ እንደኾነው፡ እንደ'አ' እና መዳረሻው እንደኾነው፡ እንደ'አ' ፊደላት። እነሆ፡ ፈጥኜ እመጣለሁ! ለእያንዳንዱም፡ እንደሥራው ፈርጄ እከፍለው ዘንድ፡ ዋጋዬ፡ ከእኔ ጋር ነው። የዚህ መጽሐፍ የትንቢት ቃል ሊፈጸም፡ ዘመኑ ደርሷልና፡ በግልጥ አውጀው እንጂ፡ አትሠውረው! እንግዴህ ወዲህ፡ ግፈኛው፡ በግፉ፥ ርኵሱም፡ በርኵሰቱ፥ እውነተኛውም፡ በእውነተኛነቱ፥ ንጹሑም፡ በንጽሕናው ይቀጥል!**" ብሎ፡ በማጠቃለያ ቃሉ እያሳሰበን እንዳስጠነቀቀን። (ራእ. ፳፪፥ ፲-፲፫።)

\+ + +